# እውነት

እውነት - ቅጽ 1፣ ቁጥር 4

የማይሸጥ

እውነትም አርነት ያወጣችኋል/ዮሐ8፡32/

ወርኃ ጥቅምት 1994 ዓ.ም.

## በወቅታዊ ዓምዶች

| | |
|---|---|
| ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ | 1 |
| እንነሣና እንሥራ | 1 |

## በቋሚ ዓምዶች

አገልግሎት



የማስታረቅ አገልግሎት 3

ቤተክርስቲያን



ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት 5

አምልኮት



የአዲስ ኪዳን አምልኮ ክፍል 2 7

በረከተ - ጥበብ

- በጸጋው ተጠራሁ 14
- ስለአንድ በደል ምትክ ሲጠፋ... 14
- እኔ «እኔ» አይደለሁም 14
- ቢሆን ኖሮ 15
- እርሱ እግዚአብሔር.. 18



የአንባቢያን ዓምድ 16



## ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ /ሉ.12፡1 /

ጌታችን በምድር ላይ ወንጌልን ያገለግል በነበረበት ዘመን በአይሁድ አምልኮ ውስጥ በእምነት ነገር ለየት ብለው ይታዩ ከነበሩት የሃይማኖት ቡድኖች መካከል ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ዋነኞቹ ነበሩ፤ እነዚህም ሰዎች በተለያየ ጊዜ ወደ ጌታ በመምጣት ትምህርቱን ይሰሙ የነበር ሲሆን በተለይም ትምህርቱን ለመወዎም የሚያስችላቸውንና ክስ ለመመሥረት የሚረዳቸውን ምክንያት ለማግኘት ሲጥሩ እንደነበር በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም እነዚህ ሰዎች የማያምኑ ከመሆናቸውም ሌላ አመለካከታቸውና አኗኗራቸው ለወደፊቱ ሥራው ጎጂ መሆኑን በመረዳቱ ይከተሉት ለነበሩት ደቀመዛሙርት «ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ» እያለ ያስተምር ነበር/ማቴ16፡6/፡፡ እንዲሁም ጌታ ይህ «የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን እርሾ» ምን እንደሆነ በተለያየ ጊዜና ስፍራ ለደቀመዛሙርቱና ለሕዝቡ አስተምሯል፡፡ ስለ እርሾው ለደቀመዛሙርቱ ካስተማረው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 16፡5-12 ላይ ያለው ለአብነት የሚጠቀስ ነው፤ በዚህ ክፍልም እርሾው የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን ትምህርት እንደሆነ ጌታ በግልጥ ተናግሯል፡፡ በሉ.12፡1 ላይ ደግሞ ጌታ የፈሪሳውያን እርሾ ግብዝነታቸው እንደሆነ ተናግሯል፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከሰዱቃውያን እርሾ ይልቅ በፈሪሳውያን እርሾ ምንነትና አሠራር ላይ እናተኩራለን፡፡ ጌታ ደቀመዛሙርቱ ከዚህ የፈሪሳውያን የሕይወት ጠባይ እንዲጠበቁ ደጋግሞ ከማስተማሩም ሌላ ለግንዛቤ እንዲያመቻቸውና ከእርሱም ለመጠበቅ እንዲያስችላቸው ለማድረግ ይህን የፈሪሳውያንን አካሄድ «እርሾ» በማለት ጠርቶታል፡፡ እንደሚታወቀው እርሾ አዲሱን ሊጥ የሚያስረጅ ነገር በመሆኑ ጥቂትም እንኳን ቢሆን ቀስ በቀስ ተጽዕኖውን እያስፋፋ ስለሚሠራ ከተጽዕኖው ለመዳን መፍትሔው ሙሉ በሙሉ መጠበቅ ብቻ ነው፡፡ የእርሾን ጠባይ ሀዋርያው ለቆሮንቶስ ሰዎች «ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን? እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ» ብሎ ከጻፈው ልም መረዳት

> ስለፈሪሳውያን «እየተናገሩ አያደርጉትም» ተባለ፤ ስለሙሴ ግን «በቃሉና በሥራውም የበረታ ሆነ» ተብሎ ተመሰከረለት/ሐዋ.ሥራ7፡22/፤ ስለ ጌታ ኢየሱስ ደግሞ «በሥራና በቃል ብርቱ» የነበረ ተባለለት /ሉ.24፡19/፡፡ ስለ እኛስ? ስለእርስዎስ? ለአንተስ? ስለ አንቺስ? ስለእናንተስ? ምን ይባል ይሆን?

(ወደ ገጽ 4 ይዞራል)

## እንነሣና እንሥራ /ነህ2፡18/

በምንኖርባት በዚህች ምድር ውስጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊሠሩት የሚችሉት ብዙ የእግዚአብሔር ሥራ አለ፡፡ እያንዳንዳችን በእድሜያችን ሙሉ ለራሳችንና ለዚህች ጠፊ ዓለም ብዙ ሥራ ሠርተን ይሆናል፤ ነገር ግን መሠራት ሲገባው ብዙ ያልተሠራ የእግዚአብሔር ሥራ እያለ ቸል ብለን የተቀመጥን ስንቶች እንሆን? በጥቅሉ ብንናገር ብዙዎች ነን ማለት ይቻላል፤ ይሁን እንጂ ሁሉም በየገዛ መንገዱ ባዘነበለበትና የራሱን ሥራ ብቻ ለመሥራት በሚሯሯጥበት፣ ለእግዚአብሔርም ሥራ ጊዜ ባልሰጠበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔር እንደ ነህምያ ያሉ የሥራ ሰዎችን በማስነሣት ሕዘቡን ለራሱ ሥራ ያነቃል፡፡

ነህምያ የእስራኤል ሕዝብ ለ70 ዓመታት በባቢሎን ምርኮ ቆይተው በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ፈድ አማካኝነት ወደ አገራቸው መመለስ በጀመሩ ጊዜ በፋርስ ዋና ከተማ በሱሳ ባለው የፋርሶች ቤተመንግሥት ውስጥ ይኖር የነበረ አይሁዳዊ ሰው ነው፤ ይህ የእግዚአብሔር ሰው በጊዜው ለነበረው አርጤክሲስ/465-424ከክ.ል.በ./ ለተባለው የፋርስ ንጉሥ ጠጅ አሳላፊ በመሆን ያገለግል ነበር/ነህ1፡11፣2፡1/፡፡ ይህም ጠጅ የማሳለፍ ሥራ የከበረ የሥራ ኃላፊነት ከመሆኑም በላይ ነህምያም በንጉሡ ዘንድና በአጠቃይ በቤተመንግሥቱ ያለውን ታማኝነትና ተወዳጅነት ያሳያል፡፡ ይህ ሥራውም የንጉሡ የቅርብ ሰዎች ከሚባሉት መካከል አንዱ አድርጎት ነበር፤ ሆኖም ነህምያ በአካል በፋርስ ቤተመንግሥት ውስጥ ይኑር እንጂ ልቡ

(ወደ ገጽ 12 ይዞራል

# እውነት ጋዜጣ

«እውነትም አርነት ያወጣችኋል» በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ ተመሥርቶ በየሁለት ወሩ የሚወጣ የክርስቲያኖች ጋዜጣ ነው፡፡

ዋና አዘጋጅ፤ መዘምር በለጠ
ም/ዋና አዘጋጅ፤ ደጉ ምሕረቴ

## መልእክተ እውነት

### የሚሰጥ በልግስና ይስጥ /ሮሜ12፡8/

ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደሆነች መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ያስረዳናል፤ ይህን የክርስቶስን አካል የሚያስገኙት ብልቶች ደግሞ አማኞች ናቸው፤ በዚህ አካል ውስጥ ያለሥራ የሚቀመጥ ብልትም የለም፡፡ ይህን እንጂ የብልቶች ሥራ አንድ ዓይነት አይደለም፤ እያንዳንዳቸው በተሰጣቸው ጸጋ መሠረት ለአካሉ መታነጽ የሚሆን ሥራን ይሠራሉ፡፡ ይህ ትምህርት ከተሰጠባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት መካከልም በሮሜ12፡4-8 ያለው ክፍል አንዱ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ «እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን» ተብሎ ከተዘረዘሩት ስጦታዎች መካከል አንዱ «የሚሰጥ በልግስና ይስጥ» የሚል ነው፤ በሌላም ስፍራ ይህ አገልግሎት ጸጋ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲ ያስረዳ «እግዚአብሔርም በቤተክርስቲያን አንዳንዶቹን.... እርዳታንም፣ አገዛዝንም... አድርጓል» ይላል /1ቆሮ12፡28/፡፡

ሕያው በሆነች በክርስቶስ አካል ውስጥ ብልት ሆነው የተገጠሙ አማኞች ሁሉ የተሰጣቸውን የብልትነት ሥራ መሥራታቸው አይቀርም፡፡ በልግስና የሚሰጡ ሰዎችም እንዲሁ ያለምንም አነሳሽ ምክንያት ለመስጠት ልባቸውም ሆነ እጃቸው የተዘረጋ ይሆናል፡፡ የሚሰጡት «ስጡ» የሚል ማሳሳቢያ ስለሚነገራቸው፣ ወይም ከሌሎች ሰዎች ዝናን ፈልገው ወይም በመስጠታቸው ምክንያት የሚመጣ በረከትን ተመቇተው ሳይሆን እንዲሁ ጸጋ ሆኖ ስለተሰጣቸው ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የሚሰጡ ሰዎች በገንዘብም ሆነ በዓይነት ስጦታን ሲሰጡ በልግስና ሊሆን ይገባል፡፡ «የሚሰጥ በልግስና ይስጥ» የሚለው ቃል ከሌላው ነገር ይልቅ አሰጣጡ በልግስና ሊሆን እንደሚገባ ይገልጻል፡፡

የልግስና ስጦታ ድሆችን በመደገፍ የሚገለጥ ሊሆን ይችላል፤ «ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ» ተብሎ በተጻፈው ቃል መሠረት በጉስቁልና ኑሮ ውስጥ ያሉትን ድሆች ልናስባቸው ይገባልና/ዕብ13፡16/፡፡ እንደዚሁም የልግስና ስጦታ ለወንጌል ሥራም ሊያገለግል ይችላል፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል ሥራን በሚሠራ በት ወቅት በገንዘባቸው የሚያገለግሉት ብዙ ሰዎች ነበሩ /ሉ8፡1-3/፤ እንዲሁም «ሁሉ አለኝ ይበዛልኛማል» እያለ ይናገር የነበረው ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ አማኞች ዘንድ ለእግዚ አብሔር ደስ የሚያሰኝ ስጦታን ሲቀበል እናያለን/ፊልጵ4፡16-18/፤ ስለሆነም ለወንጌል ሥራ እንዲውል በልግስና መስጠት እጅግ የተባረከ አገልግሎት መሆኑ ሊስተዋል ይገባል፡፡


በተሰጣቸው ጸጋ መሠረት የልግስና ስጦታን ለመስጠት የሚፈልጉ ሰዎች ምን ያህል ብንሰጥ ጥሩ ነው? በየስንት ጊዜ ብንሰጥ መልካም ነው? በማለት ማሰባቸው የማይቀር ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን ከሚያገኙት ገቢ አንድ አሥረኛውን ማለትም ዐሥራቱን እንዲሰጡ ታዝዘው ነበር/ዘሌ7፡30፤ ዘዳ12፡11፤ ሚል3፡8፤ ማቴ23፡23/፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን የዐሥራት ስጦታ አልታዘዘም፤ ይሁን እንጂ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የነበረው ድንጋጌም በልግስና የሚሰጡ ሰዎች በየሳምንቱ «እንደቀናቸው መጠን» በቤታቸው እያስቀሩ እንዲሰጡ የሚያደርግ ነው/1ቆሮ16፡1-2/፡፡ ይህ ደግሞ አማኙን ከሕግ ቀንበር ከማላቀቁም በላይ ምናልባትም በብዙ ቢቀናው ከብሉዩ ዐሥራት የሚበልጥ እንዲሰጥ ሊያደርገው የሚችል ነው፤ በጥቂቱ ቢቀናውና ያነሰ ቢሰጥ ወይም ምንም መስጠት ባይችል ደግሞ ነፍሱ አትሰቀቅም፤ የመዳን ደስታውም አይታወክም፡፡

እውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ የሚታተመውም ሆነ የሚሰራጨው የክርስቶስ አካል በሆነችው በአንዲት ቤተክርስቲያን ውስጥ ጌታ «የሚሰጡ» አድርጎ ከገጠማቸው ሕያዋን ብልቶች በሚገኝ የልግስና ስጦታ ነው፡፡ ለዚህ አገልግሎት የሚውል ማናቸውም የልግስና ስጦታ ሌሎችን የክርስቶስ ብልቶች፣ በተለይም መንፈሳዊ ጋዜጣ የማግኘትም ሆነ የፖስታ መላኪያውን የመሸፈን አቅም የሌላቸውን ወገኖች የሚያግዝ መሆኑን «በመስ ጠት» የሚያገለግሉ ሰዎች ሊረዱት ይገባል፡፡ እነዚህም በልግስና ስጦታ የሚያገለግሉ ሰዎች በሌላ ጸጋ ማለትም በማስተማር፣ በመምከር፣ በመግዛት.... ወዘተ ከሚያገለግሉ ሰዎች ጋር እኩል የሆነ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ሊገነዘቡ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ልግስናቸውን በሚሰጡበት ጊዜ ፍጹም የሆነ ደስታ ይሰማቸዋል፡፡ ልባችን ደስ ሳይለው እያዘንን ወይም በሁኔታዎች ተገደን የምንሰጠው ስጦታ ጌታን አያስደስተውም፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰ ጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፤ በሐዘን ወይም በግድ አይደለም» ብሏል/2ቆሮ9፡6/፡፡

ስለሆነም በእውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ እየተሰጠ ያለውን የወንጌል አገልግሎት በተሰ ጠው ጸጋ መሠረት «በመስጠት» ለማገዝ የሚፈልግ ማንኛውም ሕያው ብልት ሁሉ እንደቀናው መጠን፣ በልቡም እንዳሰበ በመላክ ጌታን ማገልገል ይችላል፡፡

## ሁሌም ጸደይ

አበቦችም ያብባሉ
ዘመን ቆጥረው ይፈካሉ
ለምድር ውበት ይሰጧት ዘንድ
በዝተው ደምቀው ይታያሉ
ለልብ ሐሴት ይሰጣሉ
የፍጥረት ዓይን ይስባሉ
ይዋባሉ ያስውባሉ
በጊዜያቸው ይወጣሉ፡፡
ግና.............
ምንም ቢያምር ውበታቸው
ሁሉን ቢስብ መዓዛቸው
ምድርን ቢያስጌጥ ድምቀታቸው
ቢሸፍናት ብዛታቸው
ጊዜያቸው ሲያልፍ ይረግፋሉ
ጥቂት ታይተው ይጠፋሉ
ይጠፋሉ ይሞታሉ
እስከ ጸደይ ይረሳሉ፡፡
ግና
ከዚህ ይልቅ የተሻለ
የማይጠፋ ውበት አለ
በዓለም ዘንድ የተጣለ
ቅዱሳንን ያማለለ፡፡
እርሱም.............
ከሰማያት ዝቅ ብሎ
ከምድርም ከፍ ብሎ
በደም ካባ ተሞሽሮ
ደም ግባቱ ተቀይሮ
ቢጠወልግ ቢገረጣ
ያማረውን መልኩን ቢያጣ ረገፈ
አሉ በ-ጠፋ
ሳይነሳ እንቀላፋ
ከእንግዲህ ለዘላለም
የ'ርሱ ውበት አይወራም
አበ-አሉ አከተመ
የ'ርሱ ታሪክ ተፈፀመ፡፡
የእግዚአብሔርም ነቢያቱ
የ'ርሱን ታሪክ የጻፉቱ
ባየን ጊዜ እንወደው ዘንድ
ውበት የለው የሚወደድ



የተጠላ የተናቀ
በደዌም የደቀቀ
የሕማም ሰው የመከራ
በፍጥረቱ ያልተፈራ
ሆኗል አሉ መልክ የሌለው
እኛም ክብር ያልሰጠነው፡፡



ግና...ሞትን ሽሮ ተነሳና
ሳይጠወልግ እንደገና
ለሁላችን ሆነ ተስፋ
ለዘላለም የማይጠፋ፡፡
የማይጠፋ የማይረግፍ
ሁሉ ቢያልፉ ከቶ 'ማያልፍ
እንደፈካ እንዳበበ
የፍጥረት ዓይን እንደሳበ፤
ደም ግባቱ እንዳማረ
ዘመናትን አስቆጠረ፤
ለቅዱሳን ክብር ሆነ፡፡
የሰውን ልጅ ክፉ ጠረን
በመዓዛው ቀይሮለት
ውበት ሳጣ ውበት ሆኖት
ግርማ ሞገስ ክብር ሰጥቶት
ከብሮ ደምቆ ዘሩ በዝቶ
ምድር ሰማይ ሁሉን ሞልቶ
ተቀም-ጧል በመቅደሱ
በግርማው ቀኘ በንጉሡ፡፡
ስለዚህም......
ሳይለወጥ ሳይቀየር
ለዘላለም ስለሚኖር
በውበቱ ስለሚታይ
ሆኖልናል ሁሌም ጸደይ
'ባገራችን....በሰማይ ላይ ■

እርሱ ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበን /2ቆሮ3፡6/።

# አገልግሎት

የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ/ዮሐ12.፡26/

በጌታ የተቀበልከውን አገልግሎትህን እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ /ቆላ4፡17።


## የማስታረቅ አገልግሎት/2ቆሮ5፡18-20/

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዮች የአገልግሎታቸውን ባሕርይ በሚገባ ቢያውቁ እርሱን ደስ በሚያሰኛ መልኩ ሊያገለግሉት እንደሚችሉ ግልጽ ነው። በተለያየ የጸጋ ስጦታ የሚገለጡ የተለያዩ አገልግሎቶች ሁሉም ግባቸው ጌታን ማክበርና ቤተክርስቲያንን ማነጽ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም እያንዳንዳቸው ለየራሳቸው ያላቸው የተለየ ባሕርይም ሊዘነጋ አይገባም። የወንጌል ሰባኪነት አገልግሎትም የራሱ የሆኑ የተለዩ ባሕርያት አሉት፤ ከእነዚህም ባሕርያቱ አንደኛው የወንጌል አገልግሎት የማስታረቅ አገልግሎት መሆኑ ነው።

የማስታረቅ አገልግሎት ሲባል ቀደም ሲል ፍቅርና ኅብረት የነበራቸው ወገኖች ከተጣሉ በተፈጠረው ጥል ምክንያት በመካከላቸው የሚኖረውን መራራቅና ጠላትነት አጥፍቶ ቀድሞ የነበረውን ፍቅርና ኅብረት ወደ ቦታው የመመለስ አገልግሎት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት እንደሚነግረን ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ በፊት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ፍቅርና ኅብረት ነበር። ሰው እግዚአብሔርን ሲበድል ግን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ጥል ሆነ። ሰውም የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ፤ በእግዚአብሔር ላይ በፈፀመው በደል ምክንያትም የበደሉ ክፍያ የሆነው የሞት ፍርድ ተፈረደበት፤ በአንድ ሰው ምክንያት በገባው ኃጢአት ሰው ሁሉ ይህን ፍርድ መቀበል ተገባው። ሆኖም እግዚአብሔር የማያልቅ ምሕረት እና እጅግ ታላቅ የሆነ ፍቅር ስላለው ሌላ አስታራቂ ሳይፈልግ በበደላችን ጠላት የሆንነውን እኛን ከራሱ ጋር ሊያስታርቅ ፈቀደ፤ ይህንንም የማስታረቅ ሥራ በልጁ በክርስቶስ ሆኖ ፈፀመው፤ በ2ቆሮ5፡18-20 ላይ ተመዝግቦ የምናገኘውም ለወንጌል አገልጋዮች የተሰጠው የማስታረቅ አገልግሎት ይኸው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ የፈፀመውን የማስታረቅ ሥራ የሚናገር መልእክት ከእርሱ ጋር ላልታረቁ ወገኖች ማድረስ ነው።

## በክርስቶስ የተፈጸመ የማስታረቅ ሥራ

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከራሱ ጋር ለማስታረቅ የነበረውን ፍላጎት ገና የመጀመሪያው ሰው በበደል ሲወድቅና በፊቱ ማፈር ሲጀምር እግዚአብሔር በተናገረው የፍለጋ ቃል ውስጥ እናያለን። አዳምን «ወዴት ነህ?» ብሎ በመጣራት በገነት ውስጥ ይመላለስ የነበረው ይህ የእግዚአብሔር ድምፅ፣ ምንም እንኳ ሰው ቢበድልም እግዚአብሔር ግን እንደገና ከራሱ ጋር ሊያስታርቀው በልቡ የነበረውን ምክሩን ሊያሳየን ይችላል። በእርግጥም በኋላ ዘመን የተከናወነው የኢየሱስ ክርስቶስ የቤዛነት ሥራ «ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ» መባሉን ስናውቅ/1ጴጥ10፡18-19/ እግዚአብሔር ጻድቅነቱ የሚጠይቀውን ቀጥተኛ የበደል ክፍያ ራሱ ከፍሎ ሰውን በመዋጀት ከራሱ ጋር ሊያስታርቅ በልቡ የነበረውን ዘላለማዊ ምክሩን እንደገለጠ እንረዳለን። እንደዚሁም እግዚአብሔር «ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና» የሚል ቃን ስናነብ ደግሞ ሰውን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ እግዚአብሔርን ያነሳሳው ከራሱ ፈድ በቀር ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ እንገነዘባለን/ቈላ1፡20/።

እግዚአብሔር የማስታረቅ ሥራውን የሠራው በክርስቶስ ሆኖ ነው። «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግም በታች ያሉትን <u>ይዋጅ</u> ዘንድ» ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔር ልጁን ሰው እንዲሆን ያደረገበት ዓላማ ከሕግ በታች ያሉትን <u>እንዲዋጅ</u> ነው/ገላ4፡4/፤ ምክንያቱም የማስታረቅ ሥራውን ለመሥራት በደለኛውን የሰውን ልጅ መዋጀት በጣም አስፈላጊ ነው። ትክክለኛ እርቅን ለማምጣት በደለኛ ሰው የበደሉን ዕዳ መክፈል አለዚያም ለበደሉ የሚገባውን ትክክለኛ ፍርድ መቀበል አለበት፤ እንዲህ ሲሆን ተበዳዩ በበደለኛው ላይ ያለው ጥያቄ መልስ ስለሚያገኝ እውነተኛ እርቅን መመሥረት ይቻላል። ሆኖም በደለኛው ይህን የተበዳዩን ጥያቄ መመለስ ካልቻለ ሁለቱ ወገኖች ምን ጊዜም ሊታረቁ አይችሉም። በመካከል አስታራቂ ገብቶ ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ ቢሞክርም ጥያቄው ሳይመለስ ተበዳዩ እርቁን አይቀበልም። አስታራቂውም ተበዳዩ የደረሰበትን በደል ሳይመለከት በደለኛውን ለማስታረቅ የሚያደርገው ጥረት ሕጋዊ ሊሆን አይችልም፤ በደለኛው ከተበዳዩ ጋር እንዲታረቅ በጽኑዕ ከፈለገ አስታራቂው ማድረግ ያለበት በደለኛው የተጠየቀውን ዕዳም ሆነ ካሳ ወይም ሌላ ከበደሉ ጋር የሚመጣጠን ክፍያም ቢሆን ስለ እርሱ ሊከፍልለት ይገባል፤ መዋጀት የሚባለውም ይኸው ነው፤ እንዲህ ከሆነ የሚፈልገው የማስታረቅ ሥራ ሊሠራ ይችላል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሊታረቅ የወደደው ትክክለኛው የሰው ልጅ የበደል ዕዳ ከተከፈለ በኋላ ብቻ ነው። ይህንንም ከእርሱ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊሠራው ስለማይችል ለዚሁ የመዋጀት/የቤዛነት/ ሥራ የገዛ ልጅን ወደዚህ ዓለም ላከው። ሁሉም ሰው መሞት የነበረበትን ሞት ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞተ፤ «አንድ ስለሁሉ ሞተ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ» ተብሎ እንደተጻፈው እርሱ የሞተው ሞት የሁላችንም የነበረውን ሞት ነው። በመሆኑም በእርሱ ሞት በኩል እርቅን አግኝተናል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በግልጽ ሲናገር «.....በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቻችሁ» ይላል። ይህ ክርስቶስ በሞቱ ያስገኘልን እርቅ እግዚአብሔር በእርሱ ሆኖ የሠራው የማስታረቅ ሥራ ነው፤ በሮሜ5፡9-11 ላይ «ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን። ይህም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን» ተብሎ እንደተጻፈው ለእግዚአብሔር ጠላቶች የነበርንው እኛ ለሕይወት ያበቃን መታረቅ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል አግኝተናል።

እግዚአብሔር ይህንን የማስታረቅ ሥራ ከልጁ በቀር በማንም ሊፈጽመው አልቻለም፤ በፊቱ በሚቆሙ መላእክት በኩል እንዳይፈጽመው መላእክቱንም «ስንፍና ይከሳቸዋል»/ኢዮ4፡18/ ተብሎአልና በደለኛውን የሰውን ልጅ ለማስታረቅ «አስታራቂ» ሆነው በመካከል ሊገቡ አይችሉም፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ደጋግ የእምነት አባቶችም ሆኑ እንዲሁም ነቢያትና ካህናት ይህን የማስታረቅ ሥራ እንዳይሠሩ እነርሱ ራሳቸው በደለኞች ሆነው አስታራቂ የሚፈልጉ ሰዎች ነበሩ፤ «ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ ..... ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል»/ሮሜ3፡23/

*(ወደ ገጽ 8 ይዞራል)*

**ከፈሪሳውያን እርሾ..**ከገጽ1 የዞረ

ይቻላል/1ቆሮ5፡6-7/።

በመሆኑም ከእርሾ ተጽዕኖ ለመጠበቅ መፍትሔው እርሾውን ሙሉ በሙሉ ማራቅ ብቻ ነው፤ ጥቂት ነው ተብሎም ሊናቅ አይገባውም፤ ምክንያቱም ጊዜ ይወስድበታል እንጂ «ሊጡን ሁሉ» ያቦካል። አዲስ ሊጥ የሚሆኑ የጌታ ደቀመዛሙርትም እንዲያውቁት የተፈለገው ይህንን እውነት ነው። ከሁሉም በላይ የፈሪሳውያን ግብዝነት በዚያን ወቅት አዲስ ልትመሠረት ላላት ቤተክርስቲያኑ እጅግ አስጊ እንደነበር ጌታ አውቋል።

ስለሆነም አዲሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ አዲስ እንደሆነ እንዲቆይና አዲሱ ኪዳን ያስገኘለትን በረከት እንዲያገኝም ከተፈለገ ይህ የፈሪሳውያን እርሾ በጥቂቱም እንኳን ከአዲሱ ሊጥ ጋር መነካካት የለበትም። አዲሱ ሊጥም ወደ አሮጌነት የሚለወጥ ከሆነ ደግሞ አዲስ ሊጥ እንዲኖር መድከሙ ፋይዳ አይኖረውም። ስለሆነም የዚህ ትምህርታዊ ማስጠንቀቂያ ጠሚነት በእጅጉ የላቀ ነው።

የፈሪሳውያን እርሾ ትምህርታቸውና ግብዝነታቸው እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፤ በዚህ ጥናት ግን የምንመለከተው ግብዝነታቸውን ነው። ጌታም ይህንን የፈሪሳውያንን ግብዝነት ለደቀመዛሙርቱ ብቻ ነግሮ አልቀረም፤ ለሕዝቡና ለደቀመዛሙርቱ በአንድነት አስተማረ እንጂ። በይበልጥም በማቴ23 ላይ እንደ ተጻፈልን ጌታ ስለፈሪሳውያን ግብዝነት ያስተማረው ትምህርት በጣም ሰፊና ዝርዝር ሐሳቦችን የያዘ በመሆኑ ትኩረታችንን የሚጋብዝ ይሆናል፤ ንባቡም «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው» በማለት ይጀምራል፤ በዚህም ምዕራፍ ጌታ የፈሪሳውያንን የግብዝነት ጠባይ በዝርዝር በማስቀመጥ በአንጻሩ የእርሱ የሆኑት ደግሞ ከዚያው እንዲጠበቁና በምትኩ ሊከተሉት ስለሚገባቸው መርህ «እናንተስ» እያለ እንዳስተማረ እናገኛለን። በዚህም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 በዝርዝር የተቀመጡትንና ግብዝነት የሆኑትን የፈሪሳውያንን እርሾዎች በመቀጠል እናጠናለን።

## እየተናገሩ አያደርጉትም /ቁ.3/

ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠው ነበር፤ በሙሴ ወንበር መቀመጥ ማለት በሙሴ እግር ተተክቶ በሙሴ ሥልጣንና ኃላፊነት የሙሴን ሥራ መሥራት ማለት እንደሆነ ከትውፊታቸው የሚታወቅ ነው፤ የሚያሳዝነው ግን ሙሴን ያስነሳውና ሥልጣን የሰጠው እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን በግብዝነታቸው ያንኑ ሙሴ ያስተማረውንና ያደረገውን የሚፈረን ተግባር እየፈጸሙ መኖራቸው ነው። በሙሴ ወንበር መቀመጣቸውም የሚሠሩትና የሚያስተምሩት ተቀባይነት እንዲያገኙላቸውና እነርሱም እንዲከበሩበት እንጂ በሙሴ መንገድ ለመሄድ አለመሆኑም ከዚህ ተግባራቸው ይታወቃል።

ፈሪሳውያን ለሚያስተምሩት ነገር ራስን ማስገዛት የሚችሉ አልነበሩም፤ አንድን ትምህርት ተቀባይነት ያለው የሚያደርገው ደግሞ ተናጋሪው የሚናገረውን የሚኖርበት መሆኑ ነው፤ ለሚያስተምረው ትምህርት የማይገዛ እርሱ በሥራው የገዛ ራሱን ትምህርት ያፈርሳልና። በዚህም ረገድ በኋለኛው ዘመን መንፈስ ቅዱስ «እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተመቅደስን ትዘርፋለህን? በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን?» ይላል /ሮሜ2፡21-24/። ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት ወደጎን ትተው የራሳቸውን ወግ ሲያጠብቁ ራሳቸው ሊፈጽሙት የማይችሉትን «ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ» ላይ መጫን ውስጥ ገቡ /ቁ.4/። እግዚአብሔር አድርጉት የሚለን ልናደርገው ተገቢ የሆነውን ነገር መሆኑን ልናውቅ ይገባል፤ ከዚሁ ጋርም ያን አድርጉት ያለንን የምናደርግበትን ጸጋና ኃይል ይሰጠናል፤ ፈሪሳውያን ግን ሰዎች እንዲያደርጉ የሚፈልጉትን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከባድና አስቸጋሪ ለማድረግ ቢችሉም ያንኑ እንዲደረግ የሚፈልጉትን ሥራ ራሳቸው ግን ሊፈጽሙት አይችሉም ነበር፤ ሌላውም ይሸከመው ዘንድ ኃይልን ሊሰጡት አይችሉም።

በተመሣሣይ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ለራሳቸው በልባቸው ቅድስና ሳይኖራቸው ሰው በሚበላው ነገር እንኳን ሳይቀር ይረክሳል በማለት «አትንካ፣ አትቅመስ»/ቈላ2፡22/ የሚሉ፣ ራሳቸው በተሸነፉበት መንገድ ሌላው እንዲሄድ የሚያበረታቱ እየበዙ መጡ እንጂ ከሕዝብ መካከል ሊታጡ አልቻሉም፤ ስለይቅርታ የሚሰብኩ ነገር ግን መታረቅ ያቃታቸው፣ ስለ አንድነት የሚያወሩ ነገር ግን መኀራበት የተሳናቸው፣ ለምን ከዚህ ደረስን ቢሉ መልሱ አንድ ነው፤ እርሾው የሚል። የትናንቱን ከዛሬ የሚለየው ነገር ቢኖርም እርሾው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ቀደምት ነን ባዮችን ወርሶ አዲስ ነን ባዮቹን ማዳረሱ ነው። የሚያምነውን የማይናገር፣ የሚሰብከውን የማይተገብር፣ በተራራና በዋሻ ውስጥ በድንጋይና በድንጋይ መካከል ስለመሹለክ የሚያስተምር ለራሱ ግን በሜዳ እንኳ መሄድ የሚሳነው ቢኖር እርሱ በፈሪሳውያን ግብዝነት የተያዘ ነው፤ እግዚአብሔር ከሰው ከሚጠብቀው በላይም በሰው ላይ ሸክምን የሚጭን እንዲሁ በዚህ ግብዝነት ተሞልቷል። ይሁን እንጂ ይህን እርሾ መድፋት ይቻላል፤ ይኸውም የምናምነውንና የምንሰብከውን ከሰኞ እስከ እሁድ ስፍራና ጊዜ ሳንለይ ተግባር ላይ በማዋል ነው። ለጸሎት ስንሰበሰብ የምንለውና የምንሆነው ከመኖሪያ ቤታችን፣ ከመሥሪያ ቤታችን፣ ከትምህርት ቤታችን ካልዘለቀ በእርግጥ በዚህ እርሾ መለወሳችን ሊዘነጋ አይገባም። በሌላ በኩል ደግሞ በአንደበታችን ከምንሰብከው በላይ በኑሮአችን የምንሰብከው ይበልጥ ፍሬ የሚያፈራና ጌታንም ደስ የሚያሰኝ እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል።

ስለፈሪሳውያን «እየተናገሩ አያደርጉትም» ተባለ፤ ስለሙሴ ግን «በቃሉና በሥራውም የበረታ ሆነ» ተብሎ ተመሰከረለት/ሐዋ.ሥራ7፡22/፤ ስለ ጌታ ኢየሱስ ደግሞ «በሥራና በቃል ብርቱ» የነበረ ተባለለት /ሉቃ24፡19/። ስለ እኛስ? ስለእርስዎስ? ለአንተስ? ስለ አንቺስ? ስለእናንተስ? ምን ይባል ይሆን?

## ስለውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ/ቁ.5/

ይህ ደግሞ ሌላው የፈሪሳውያን የግብዝነት እርሾ ነው። እነዚህ ሰዎች የሚያስተምሩትን የማያደረጉ ብቻ ሳይሆኑ የሚያደርጉትንም እንኳ ለሰው እንዲታዩ የሚያደርጉ ነበሩ። ይህም ብድራትን ወይም ምስጋናን ከሰው ለመቀበል ወይም በዚያ በሚያደርጉት በሰው ዘንድ ከበሬታን ለማግኘት ከመፈለግ የሚመጣ ነው። ጌታ ዳግመኛም በሌላ ቦታ እንደዚህ ካሉ ሰዎች አድራጎት እንድንጠነቀቅ የሚከተለውን ያስተምረናል፤ «ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም፤ እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከብሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል፤ አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል»/ማቴ6፡1-4/። ጌታ ከዚህም በተጨማሪ «ስትጸልዩ እንደግብዞች አትሁኑ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ አንተ

*(ወደ ገጽ 8 ይዞራል)*

ኀበ ሀለዉ ክልኤቱ
ወሠለስቱ ጉቡኣን
**በስምየ**
ህየ ሀለውኩ አነ
ማዕከሎሙ
/ማቴ18፡20/

# ቤተክርስቲያን



ሁለት ወይም ሦስት
**በስሜ**
በሚሰበሰቡበት
በዚያ በመካከላቸው
እሆናለሁ
/ማቴ18፡20/

## ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት

በእውነት ጋዜጣ ቁጥር 3 እትም ላይ ቤተክርስቲያን ከማቴ18 አንፃር በምድርና በሰማይ ያላትን ገጽታ በሰፊው ተመልክተናል፤ በዚህ እትማችን ደግሞ ቤተክርስቲያን በሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክታት ከተገለጠ ችባቸው ትምህርቶች ውስጥ የክርስቶስ አካል እንደሆነች የሚናገረውን እውነት እንመለከታለን።

### የአካል ምንነት

ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል መሆኗን ለመረዳት እንችል ዘንድ የአካልን ምንነት በቅድሚያ ማየት ይኖርብናል። በመጀመሪያ አካል ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ለመረዳት ከሚያስችሉን ምንባቦች አንዱ ስለቤተክርስቲያን «አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት» ተብሎ የተነገረው ነው/ኤፌ2፡23/፤ በዚህም መሠረት ለክርስቶስ አካሉ የምትሆን ቤተክርስቲያኑ ለእርሱ ሙላቱ ናት፤ ወንጌል በምድር ላይ በተሰበከ ጊዜ ሁሉ በየስፍራው ቤተክርስቲያን ስትታይ በዚያ በታየችበት ስፍራ ክርስቶስን ትገልጣለች፤ ወደሰማያት የወጣው ጌታ ኢየሱስም በቤተክርስቲያኑ በኩል በምድር ላይ ራሱን ይገልጣል፤ ከዚህ አንጻር ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት ስንል የክርስቶስ መገለጫው ናት ማለታችን ነው።

የአካልን ምንነት የሚገልጠው ሌላው እውነታ ደግሞ በ1ቆሮ12፡13 ላይ «አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና» ተብሎ የተጻፈው ነው፤ ከዚህም በመነሣት አካል ማለት የብልቶች ስብስብና ኅብረት ማለት ይሆናል፤ ይህም በሰው አካል ምሳሌነት የተገለጠ እውነታ ነው፤ «በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን......»/ሮሜ12፡4/ ተብሎ እንደተፃፈው በጌታ ኢየሱስ የሚያምኑና ወደ አካሉ በመንፈስ ቅዱስ አንድ ይሆኑ ዘንድ በየጊዜው የተጨመሩ ሁሉ ያለመለየት እያንዳንዳቸው የክርስቶስ አካል ብልቶች ናቸው። ስለዚህ አማኞች በየግላቸው ብልቶች የሆኑባት በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም የተመሠረተችው ብቸኛዋ የአማኞች ጉባኤ ማለት ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ነው።

### የአካል መገኘት

የአካልን ምንነት ከላይ በተገለጠው መልኩ ከተረዳን ለመሆኑ የክርስቶስ አካል የምትሆን ቤተክርስቲያን መቼ ተገኘች? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ከቅዱሳት መጻሕፍት እውነታ ለመረዳት እንደሚቻለው የክርስቶስ አካል ቤተክርስቲያን እውን የሆነችውና የተገኘችው ጌታ «በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል...... ይህንን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም

> «....ነገር ግን ብልቶች እርስ በእርሳቸው በትክክል ይተሳሰቡ ዘንድ እንጂ በአካል መለያየት እንዳይሆን ..... እግዚአብሔር አካልን አገጣጠመው»
> /1ቆሮ12፡25/

ነበርና»/ዮሐ7፡36-37/ ብሎ እንደተናገረ ጌታ ኢየሱስ ከከበረ በኋላ መንፈስ ኢየሱስን ለሚያምኑ በተሰጠ ጊዜ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። ጌታ ከመሄዱ በፊትም «እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ»/ዮሐ16፡7/ ብሏል፤ እንደዚሁም ጌታ በምድር ላይ በማይኖርበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሊሠራ ያለው የራሱ ሥራ እንዳለው፣ ለዘላለምም ከእነርሱ ጋር እንደሚኖርና፣ እርሱ የነገራቸውንም ቃል እንደሚያስታውሳቸው፣ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸውና በተለያዩ ጉዳዮችም ላይ እንደ ሚደግፉቸውና እንደሚያበረታቸው በግልጽ ነግሮአቸዋል። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ ከእነዚህ ሁሉ የሚቀድምና የሚጠበቀው ሌላ ሥራ ነበረው፤ ይኸውም ጌታ ለደቀመዛሙርቱ «ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃችሁ»/ሐዋ.ሥራ1፡5/ ብሎ በነገራቸው መሠረት ያመኑትን ሁሉ ወደ አንድ አካል አጠምቆ ሰማያዊት የምትሆን ቤተክርስቲያንን ማስገኘት ነበር፤ መንፈስ ቅዱስ ይህን የእርሱ ብቻ የሆነውን ሥራ ለመፈጸም ሲመጣ አስቀድሞ አብ በተራራ ላይ ሕግን በሰጠ ጊዜ የተራራው ራስ እንደጤሰ፣ የወልድም የመወለዱ ብሥራት በመላእክት ዝማሬና በሰማይ ከዋክብት ምልክትነት እንደታጀበ፣ የእርሱም ወደ ምድር መምጣት በታላቅ ድምጽና በተከፋፈሉ ልሳኖች መታየት የተመሰከረ ነበር፤ በዚሁ መሠረት የክርስቶስ አካል ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘችው በዚህ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ሁሉ ወደ አንድ አካል ሊያጠምቅ በታላቅ ምልክት ታጅቦ በመጣበት ዕለት እንደሆነ እንረዳለን። እዚህ ላይ በሚገባ ማስተዋል የሚኖርብን እውነት ቢኖር ከሕግና ከኢየሱስ ወደዓለም መግባት ጋር የተያያዙት ምልክቶች ተደግመው እንደማያውቁ ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት ጋር የተያያዙት ምልክቶችም አንድ ሰው በጌታ በኢየሱስ ባመነ ቁጥር ተደግመው የሚታዩ አለመሆናቸውን ነው፤ ምክንያቱም ይህ የአንድ ጊዜ ብቻ ክስተት ስለሆነ መንፈስ ቅዱስም በዚህ ዘመን ይህን እንዲያደርግ አይጠበቅበትም። ይሁን እንጂ አንድ ሰው በጌታ ኢየሱስ ሲያምን ከላይ የተጠቀሱት በዓይን የሚታዩ ክስተቶች ሳይኖሩ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ያድራል፤ አስቀድሞ ወዳለችው ወደ አንዲቱ የክርስቶስ አካልም ይጨምረዋል፤ ከክርስቶስ ጋርም ኅብረት ይሰጠዋል/ሐዋ.ሥራ5፡14/። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ቤተክርስቲያን ከምድር እስክትወሰድ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል። ይህንን እውነታ ከመንፈስ ቅዱስ ሌላ የሚሠራው ፍጥረታዊ እጅ ካለመኖሩም ሌላ ይህም መጨመር ወይም ወደ አካሉ መግባት አንዴ ከተከናወነ በኋላ በምንም ዓይነት መልኩ አይደገምም።

### የአካል ራስና ተግባራዊ እንቅስቃሴ

እንግዲህ የክርስቶስ አካል ምንነት የራሱ የክርስቶስ መገለጫ፣ እንዲሁም የብልቶች ስብስብ ወይም ኅብረት ነው ካልን ይህንን አካል የሚመራ አንድ መሪ ያስፈልጋል፤ በዚህ ብቸኛ መሪ መመራቱም አካልን አካል ያሰኘዋል፤

(ወደ ገጽ 6 ይዞራል)

## ቤተክርስቲያን.. ከገጽ 5 የዞረ

በክርስቶስ አካል ብልት የሆነ አማኞም ይህንን ሊረዳ ይገባዋል::

ሐዋርያው ጳውሎስም በ1ቆሮ12 ይህንን እውነታ ለማስረዳት የተጠቀመበት የሰው አካልም አማናዊ ለሆነችው የክርስቶስ አካል ተገቢ ምሳሌ ነው፣ አንድ ሰው የአካሉን ማናቸውንም ብልቶች ለማንቀሳቀስ ከፈለገ የአካሉ ራስ ማለትም አእምሮው ለብልቶቹ ትዕዛዝ መስጠት የግድ ይኖርበታል፣ ራስ የማያውቀው ጤናማ ብልት አካል ውስጥ ፈጽሞ ሊኖር አይችልምና ከራስ በሚቀበለው ትእዛዝ ይንቀሳቀሳል፣ እንዲሁም «የክብር አምላክ..... ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት፣ ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተክርስቲያን ሰጠው» ተብሎ እንደተጻፈው እግዚአብሔር ራስ እንዲሆናት ክርስቶስን ለቤተክርስቲያን ሰጠ/ኤፌ.1፡23/:: በዚህ ጥቅስ መሠረትም ኢየሱስን ለቤተክርስቲያን ራስ እንዲሆን የሰጠው ወይም የወሰነው እርሱ የክብር አምላክ ነው:: ምናልባት እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ አደረገ? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችል ይሆናል፣ ለዚህም መልሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ምድር ሐዋርያ ሆኖ የተላከው ጌታ ኢየሱስ የአባቱን ፈድ በመፈጸም እርሱ ደስ የሚሰኝበትን በማድረጉ፣ ከተቀበለው መከራ ፍጹም መታዘዝን በመማሩና በብዙ ወንድሞችም መካከል በኵር በመሆኑ ራስ ሊሆን ቻለ የሚል ይሆናል፣ ምክንያቱም በለበሰው ሥጋ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ያለ እንከን የፈጸመና ስለሌሎች ራሱን ለሞት እስከመስጠት በእግዚአብሔር ፊት በምድር ላይ ካሉ ቅዱሳን ከሚባሉትና ሥጋ ከለበሱት ሰዎች መካከል ሁሉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ የቆመ እርሱ ብቻ ነውና::

እንግዲህ አንባቢ በጌታ ፍቅር እንዲያስተውል የሚፈለገው እውነታም ያለው እዚህ ላይ ነው፣ ክርስቶስ ራስ እንዲሆን የወሰነውና እንዲህ እንዲሆን ያደረገው እግዚአብሔር ከሆነ ይህንን የእግዚአብሔርን ስጦታና ውሳኔ መቀበል የዳነ አማኞ ሁሉ እውነተኛ መታዘዝ ሊሆን ይገባል፣ ከዚህ በማያያዝም እያንዳንዱ አማኞ ብልት እንደመሆኑ መጠን ከሌሎች አማኞች ጋር ደግሞ በአንድነት ሕያው የሆነችውን አንዲቱን የክርስቶስን አካል ማስገኘቱን በውል ይረዳል፣ አካልም ያለ ራስ ሙት መሆኑን ያስተውላል፣ የቤተክርስቲያን ራስ ናቸው ብሎ ከሚያስባቸው ሰዎች ላይም ዓይኖቹን ያነሳል፣ ለእያንዳንዱ ብልትም ሆነ በጋራ ለሁሉም አማኞች ብቁ መሪ ሊሆን ለሚችለውና ሁሉንም ብልቶች /አማኞች/ እርሱ በፈቀደላቸው የጸጋ ስጦታ ሊያንቀሳቅስ ለሚችለው ራስ ብቻ ይታዘዛል፣ ጌታ እግዚአብሔር ክርስቶስን ራስ እንዲሆን ለቤተክርስቲያን እንደሰጠው ለአካሉም መሪና ራስ እርሱን ብቻ እንዳደረገው ያምናል፣ እውነትን እየወደደ ዓመፃንና ያለመታዘዝን በእውነት ሏ እየተዋመ ይህንን እውነት የሚዋም የሰዎች ራስነት ጎልቶ ከሚነገርበትና ከሚታይበት ክርስትና መሰል ምድራዊ ስብሰባ ይርሏ፣ መሪህ ማነው? ብለው ለሚጠይቁትም ሁሉ እንደ ሐዋርያው «እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው» በማለት መሪው ክርስቶስ እንደሆነ ይመሰክራል/ቈላ1፡18/፣ እንደእርሱ ልገታ አካል ብልት በሆኑት አማኞች ላይም ራስ ለመሆን አይነሳሳም፣ የሌሎች ሰዎችንም ራስነት አይቀበልም::

## የራስና የአካል አንድነት

የዚህን ርእስ ዋና ሐሳብ ማንኛውም አማኞ በቀላሉ ለመረዳት የሚቸገር አይመስለንም፣ ምክንያቱም በራስና በአካሉ ብልቶች መካከል ያለውን ቅርብ ትስስር የሚገልጽ በቂ ማስረጃ ከገዛ ሰውነቱ ሊያገኛ ይችላልና፣ የሰው «ራስ» ዝቅ ብሎ ከሚገኘው የአካል የመጨረሻ ክፍል የእግር ጣት ጋር እጅግ በሚደነቅ ሁኔታ በጅማት ተያይዞአል፣ ከዚህ መያያዝ የተነሣም በእግር ጣት ላይ የሚደርስ ጥቂቱ ጉዳት የ«ራስም» ጉዳት ይሆናል፣ ጥቂቱም የአንድ ብልት መክበር ወይም ደስ መሰኘት የ«ራስም» ደስታ ነው:: አማናዊ የሆነች ሕያዊት ቤተክርስቲያንም ራስ ከሆነላት ጌታ ጋር ያላት እውነተኛ ግንኙነት ይህንን ይመስላል:: ክርስቶስ ኢየሱስ ጥቂቱ የአማኞች ጉዳት የእርሱ ጉዳት እንደሆነ ይቆጥረዋል፣ ይሰማዋልም፣ ለዚህም በሐዋ.ሥራ9፡1-9 ላይ ሳውል የጌታን ደቀመዛሙርት በሚያሳድድበት ጊዜ ጌታ «ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?» በማለት ራሱን ከሚሰደዱት አማኞች ጋር መቁጠሩን ማስታወሱ በቂ አብነት ነው::

ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ ርእስ እንደገና በሚገባ ልናጤነው የሚያስፈልግ ሌላ እውነት ስላለ ልባችንን ይበልጥ ለሉ እውነት እንድንከፍት እየተጋበዝን በማስተዋል ወደዚህ እውነታ ዳርቻ እንድንደርስ እንጠየልን:: ይህም እውነታ የአካልና የራስ በቁጥር አንድ መሆን ነው፣ ማንም ሰው አንድ ራስ አለው፣ እንዲሁም አንድ አካል ብቻ አለው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ሲመሰክር «አንድ አካልና....አንድ ጌታ» ይላል /በኤፌ4፡4/፣ ሐዋርያው ይህንኑ አባባሉን በ1ቆሮ12፡12-13 ባለው ክፍል ሲያብራራው ደግሞ «አካልም አንድ እንደሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ ክርስቶስም ደግሞ እንዲሁ ነው» ብሏል፣ እንግዲህ እነዚህን ሎች መነሻ አድርገን የዚህን እውነት ብርሃን ማየት ከቻልን በቀላሉ ሉ እየነገረን ያለው «አንድ ራስ ካለ መኖር ያለበት አንድ አካል ብቻ ነው» የሚል ነው፣ አንድ አካልም ካለ መኖር ያለበትም አንድ ራስ ብቻ ነው፣ ስለዚህ አይሁድም ብንሆን ወይም የግሪክ ሰዎች ወይም ባሪያዎችና ጨዋዎች ብንሆን ተፈጥሮአዊ የመኖሪያ ስፍራዎቻችን የማያገናኙንና በእጅጉ የተራራቅን ብንሆን እንኳን ለሁላችንም አንድ ራስ አለን፣ እርሱም ጌታ ኢየሱስ ነው፣ እኛም በፍጹም አንድ አካል /ቤተክርስቲያን/ ብቻ ልንሆን እንጂ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆነ አካል ልንሆን ከቶውንም አንችልም፣ የእግዚአብሔር ሏም ከአንድ በላይ አካል እንዳለ አያሳየንም::

ቤተክርስቲያን አንዲት ከሆነች በዘመናችን የተለያየ ቅጽል ስያሜ በመያዝ «ቤተክርስቲያን» ተብለው የሚጠሩ ብዙ የእምነት ድርጅቶች ስለምን በዙ? ብለን አንዳንዶቻችን መጠየቻን አይቀሬ ነው:: ይህ ግን በውል የጌታን ራስነትና የአካሉንም አንድነት ከመካድና በሥጋዊ አስተሳሰቦች ከመመራት የተፈጠረ መሆኑን እየገለጽን በዚህ ዙሪያ «ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም» በሚል ርእስ በቁ.2 ጋዜጣችን ላይ ያቀረብነውን ጽሑፍ እንዲመለከቱ እንጋብዛለን::

## የብልቶች ሥራ

በአካል ውስጥ ብዙ ብልቶች እንዳሉ ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል፣ እነዚህ ብዙ የሆኑ ብልቶች እንደ ልዩነታቸው በአካል ውስጥ የሚሠሩትም ሥራ የተለያየ ሲሆን ይህም ሥራ አስቀድሞ ይገለጡበት ዘንድ በተወሰነላቸው መሠረት ነው፣ ለምሳሌ እጅ የእጅን ሥራ ከመሥራቱ በፊት እጅ ሆኖ መዘጋጀት ወይም መፈጠር ነበረበት:: ሕያዊት የክርስቶስ አካል በሆነች ቤተክርስቲያንም ያለው እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም፣ በጌታ ዘላለማዊ ምርጫ ወደ ደኅንነት የተጠራ አማኞ በመንፈስ ቅዱስ ወደ አካሉ ከተጨመረ ጊዜ ጀምሮ በተወሰነለት የብልትነት ስፍራ ብቻ መገለጥ ይጀምራል፣ በዚህ ጊዜ እኔነት ስፍራውን ለቆ፣ ብልቶችም በተገቢው መንገድ በአካሉ ውስጥ ያላቸው ድርሻ እውን እየሆነና ጌታም ብቻ ራስ መሆኑን እየገለጠ ይመጣል:: ዛሬ ግን ይህንን ክቡር እውነታ ባለመረዳት ራስ የሆነው ክርስቶስ ሳይሰጣቸውና ሳይወስንላቸው በግል ፈቃቸው ይህ ጸጋ አለን ብለው የሚናገሩ ስንቶች ይሆኑ? ስንቶችስ ይህን ጸጋ እፈልጋለሁ፣ ያንኛውን አልሻም እያሉ ጌታ እንደወደደ ሊሰጥ ባለው ጸጋ ላይ ባለመብት እንደሆኑ ራሳቸውን ቆጥረው ይሆን? ስንቶችስ የቤተክርስቲያን ራስ የሚሆን ጌታ በአካሉ /በቤተክርስቲያኑ/ ውስጥ ብልቶቹ የሆኑ አማኞችን እንደሚያዝዝና እንደሚያንቀሳቅሳቸው ባለማስተዋልና የስጦታ ምንጮች እነርሱ

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

…በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ …ነው እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚልፈገው ምንድር ነው?

# አምልኮት

እኛ በመንፈስ እግዚአ ብሔርን የምናመልክ
በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን…ነንንና:: /ፊልጵ3፡3/

## የአዲስ ኪዳን አምልኮ - ክፍል 2

በቁጥር 3 የእውነት ጋዜጣ በአምልኮ ዓምድ ሥር «የአዲስ ኪዳን አምልኮ» በሚል ርእስ በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚ አብሔር የሚፈልገው አምልኮ ምን ዓይነት እንደሆነ ጠቅለል ባለ መልኩ ተመልክተናል:: አብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱለትን ሰዎች እንደሚፈልግ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል ተብራርቷል:: ያለንበት ዘመንም ጌታ «ይመጣል» ብሎ የተናገረለት በመንፈስና በእውነት የሆነው አምልኮ የሚፈጸምበት ጊዜ እንደሆነ ተገልጧል:: በዚህ እትም ደግሞ መንፈስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር የሚጣጣመውን ይህን የመንፈስ አምልኮ ተግባር ላይ እንድናውለው ከጌታ የተሰጠውን የአምልኮ መመሪያ እንመለከታለን::

«እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱስትም በመንፈስና በእውነት ሲሰግዱስት ያስፈልጋቸዋል»/ዮሐ4፡24/::

በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር የሚመለክበት መንገድ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ይመለክበት ከነበረው መንገድ በእጅጉ ይለያል፤ በብሉይ ኪዳን ማናቸውም አገልግሎት ይፈጸም የነበረው በብዙ ዝርዝር ሥርዓትና የዚህ ዓለም በሆነ ምድራዊ መቅደስ በመገልገል ነበር:: የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን ሲገልጥ «ፊተኛይቱም ደግሞ <u>የአገልግሎት ሥርዓት</u> እና <u>የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ</u> ነበራት» ይላል /ዕብ9፡1/፤ አዲስ ኪዳን ግን ከዚህ በተለየ መልኩ በመንፈስ የሚፈጸም አገልግሎት አለው:: ይህም «እርሱ ደግሞ <u>በመንፈስ</u> እንጂ በ<u>ፊደል</u> ለማይሆን ለ<u>አዲስ ኪዳን</u> አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን» ተብሎ ተገልጧል/2ቆሮ5፡6/፤ በብሉይ ኪዳን የነበረው ፊደላዊ የሆነ የአገልግሎት ሥርዓትና በምድራዊ ቤተመቅደስ ይቀርብ የነበረው አምልኮ ለሰማያዊና ለመንፈሳዊ ነገር ምሳሌና ጥላ ከመሆን ባሻገር የእግዚአብሔርን መሻት የሚያሟላ አልነበረም/ዕብ8፡5/፤ እግዚአብሔር ግን መንፈስ ነው፤ ስለሆነም በመንፈስና በእውነት የሚቀርብ አምልኮን ይሻል/ዮሐ4፡23-24/:: የብሉይ ኪዳን ዘመን ነገሮች ሁሉ ፊደላዊና ዝርዝር የአገልግሎት ሥርዓትን የተከተሉ እንጂ በመንፈስ የሚፈጸሙ ባለመሆናቸው ይህን የእግዚአ ብሔርን መሻት የሚያረኩ አልነበሩም:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ከመጣ በኋላ እግዚአብሔር በመንፈስና በእውነት የሚመለክበት ጊዜ ደርሷልና ሰዎች በዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል:: ጌታ ኢየሱስ «የሚሰግዱለት ሁሉ በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል» ብሎ ሲናገር በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ መፈጸም ያለበትን ዋነኛና መሠረታዊ የሆነ የአምልኮ መመሪያ መስጠቱ መሆኑን ልናስተውል ይገባል፤ «ያስፈልጋቸዋል» የሚለው የማሰሪያ አንቀጽ ጌታ የተናገረው ይህ ቃል «መመሪያ» እንደሆነ ያሳያልና::

> አምልኮ አማኞች በሙሉ እንደአሮን ልጆች ሆነው በጌታ ዙፋን ተሰብስበው ጌታ ደግሞ በመካከላቸው እንደአሮን ሆኖ እየመራ የሚፈጸም የመንፈስ አገልግሎት ነው፤

ስለሆነም ጌታችንና መምህራችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ ባስቀመጠልን የአምልኮ መመሪያ መሠረት መንፈስ ለሆነው እግዚአ ብሔር የሚሆን በመንፈስና በእውነት የሚፈጸም አምልኮ ልናቀርብ ይገባናል:: በአምልኮ ጊዜ ማሰብ ያለብን እኛ የምንፈልገውን ሳይሆን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነው፤ እንደዚሁም ማተኮር ያለብን ለእኛ ደስ በሚያሰኘን የአምልኮ አፈጻጸም ላይ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ደስ በሚያሰኘው ላይ ነው::

እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ማምለክ ሲባል ከዝርዝር የአገልግሎት ሥርዓት፣ ከቁሳዊ የመገልገያ ዕዎችና ከሥጋ ስሜቶች ተለይቶ ከልብ በሆነ እምነት ማምለክ ማለት ነው:: ይህም ዳግም የተወለደው የአዲሱ ሕይወታችን አንዱ መለያ ባሕርይ ነው:: የአዲስ ኪዳኑ እውነት ይህ ሆኖ ሳለ በዘመናችን በብሉይ ኪዳንና በዓለማዊነት ተጽዕኖ ሥር የወደቀ አምልኮ ሲፈጸም በብዙ ስፍራዎች ይታያል፤ ዝርዝር የአገልግሎት ሥርዓት፣ ቁሳዊ የመገልገያ ዕዎችና የሥጋ ስሜቶች ብዙ የአምልኮ ጉባዔያትን ተቆጣጥረው ይገኛሉ፤ ከእነዚህ አንዳንዶቹ ወደ ተሻረው አምልኮተ ኦሪት ባፈገፈጉ ሰዎች አማካኝነት ከብሉይ ኪዳን የተቀዱ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከዓለምና ከአምልኮተ አሕዛብ የተኮረጁ ሆነው እናገኛቸዋለን፤ ምንም እንኳን እነዚህ ነገሮች ለረጅም ጊዜ በስፋት ተቀባይነት አግኝተውና በሰው አሠራር ውስጥ ተለምደው ብንመለከታቸውም በክርስቶስ የአምልኮ ትምህርት ውስጥ የማይገኙ እስከሆኑ ድረስ ከአምልኮአችን ልናስወግዳቸው ያስፈልጋል፤ ለዚህም ይረዳን ዘንድ በጉባኤ አምልኮ ጊዜ በመንፈስና በእውነት <u>ያልሆኑትን</u> የሰው ሥርዓቶችንና ልምምዶችን በመዘርዘር የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረንን እውነት ቀጥሎ እንመለከታለን::

### አምልኮን የሚመራ ሰው መመደብ

የጉባዔ አምልኮ በሚፈፀምበት ጊዜ ከሚታዩት የሰው ሥርዓቶች አንዱ አምልኮውን የሚመራ ሰው መመደብ ነው፤ ይህም አምልኮን የሚመራ ሰው አንዳንድ ጊዜ በዘልማድ በተወሰኑት ዘንድ «ሠራኢ ቄስ»፣ በሌሎች ዘንድ ደግሞ «አስመላኪ» ተብሎ ይጠራል:: «ሠራኢ ቄስ» የሚባለው በብሉይ ኪዳን ይደረግ እንደነበረው ከሕዝቡ የተለዩ ሰዎችን የካህናት ወገን በሚያደርገው ሥርዓት የሚመደብ የአምልኮ መሪ ሲሆን «አስመላኪ» ደግሞ በዓለማዊው መድረክ «ኮንዳክተር ወይም ፕሮግራም መሪ» ተብሎ የሚጠራውን ሰው ባሕርይ የተላበሰ፣ የንግግርና የአቀናባሪነት ችሎታ ያለውና ሌሎች ሲያመልኩ እርሱ እንዲያስመልክ ከሚያመልኩት ሰዎች ተለይቶ የሚመደብ ሰው ነው::

በብሉይ ኪዳን ከእስራኤል ሁሉ ተለይተው አምልኮን የሚመሩ ሰዎች ከአሮን ወገን የሆኑት ካህናት ብቻ ነበሩ፤ ለካህናቱም ሊቀ ካህናት ነበራቸው፤ እነዚህ ካህናት በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ሥርዓተ አምልኮውን የሚያካሂዱት ዘወትርና በየበዓላቱ ነበር፤ በሙሴ ዘመንም አሮንና ልጆቹ ይህንን የክህነት ሥራ ይሠሩ ነበር/ዘጸ28፡1/፤ በአምልኮው ውስጥ ካላቸው አገልግሎት መካከልም ዋና ዋናዎቹ በየቀኑ ሁለት ጠቦቶችን ለሚጠል መሥዋዕት ማቅረብ፣ በዕጣን መሠዊያው ላይ ጣፋጭ ዕጣን ማጠንና ከማታ እስከ ማለዳ የሚቆይ መብራትን ማብራት ናቸው/ዘጸ29፡38-30፡8/፤ እነዚህ ካህናትም ሲሾሙ ሰውነታቸውን ይታጠባሉ፤ የተለየ ልብሰ-ተክህኖም ይለብሳሉ፤ የቅብዓት ዘይትም ይፈስባቸዋል /ዘሌዋ8፡1-13/፤ በዚህ መልክም የአሮን ወገኖች ከሕዝቡ

ወደ ገጽ 11 ይዞራል

## የማስታረቅ.. ..ከገጽ 3 የዞረ

ተብሎ እንደተጻፈው በኃጢአትና በበደል ተጠያቂ ያልሆነ አንድም ሰው አልነበረም:: ስለሆነም እግዚአብሔር ኃጢአት የሌለበት አስታራቂ በመፈለጉ ኃጢአት ያላወቀውን ልጁን ወደዚህ ዓለም ላከው/2ቆሮ5፡21/::

ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበሩ እስራኤልና እግዚአብሔርን የማያውቁ አሕዛብ በዚህች ምድር ላይ ነበሩ:: የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤል ከአሕዛብ ይልቅ ከእግዚአብሔር ጋር የማያገናኛቸውና የተቀደሰ ሕዝብ ያደረጋቸው ሕግ ነበራቸው፤ ነገር ግን ሕጉ የነበረውን ጥል አስወግዶ እነርሱን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቻቸው አልቻለም:: አሕዛብ ደግሞ ከእግዚአብሔር እጅግ ርቀው የነበሩ ናቸው:: በዚያውም ላይ በእስራኤልና በአሕዛብ መካከል በሕጉ ምክንያት ምንም ዓይነት ኅብረትና አንድነት አልነበረም:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ እስራኤልና አሕዛብን ሁለቱን በአንድነት በሞቱ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ፤ ስለዚህም የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል «እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተናገሩትንም የትእዛዛትንም ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስ ሰው ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው» ይላል/ኤፌ2፡14-16/::

እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ የሠራው ይህ የማስታረቅ ሥራ በምድር ላይ ላለ የሰው ዘር ሁሉ የሚሆን ነው፤ ማንም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምን ከሆነ አሁንም የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል/ዮሐ3፡36/፤ ያ ኢአማኒ አይሁዳዊም ሆነ አሕዛባዊ ገና ከእግዚአብሔር ጋር ያልታረቀና አሁንም የእግዚአብሔር ጠላት የሆነ ሰው በመሆኑ አሁንም አስታራቂ ይፈልጋል:: በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ /አስታራቂ/ ደግሞ አንድ እርሱም ኢየሱስ ብቻ ነው፤ ይህም እውነት «በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» ተብሎ በግልጽ ተነግሮናል/1ጢሞ2፡5/:: ስለሆነም በዚህም ዘመን ከተስፋው ቃል ርቀው ያሉትንና በቁጣው ሥር የሚገኙትን ኢአማንያን እግዚአብሔር ከራሱ ጋር የሚያስታርቀው ብቸኛ መካከለኛ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው:: ሰዎችም በእርሱና እርሱ በሠራው የማስታረቅ ሥራ ሲያምኑ እርቁ ይፈጸማል::

## በመልእክተኞቹ በኩል የሚፈጸም የማስታረቀ አገልግሎት

እግዚአብሔር በመስቀል ላይ በክርስቶስ የፈፀመው የማስታረቅ ሥራ በየዘመናቱ አይደጋግምም፤ ኢየሱስ አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል /ዕብ10፡12/፤ ለዕርቁም የሚያስፈልገው የደም ዋጋም የተከፈለው በዚሁ በአንዱ ዘላለማዊ መሥዋዕት ነው፤ ዕርቁም በዚያው በመስቀል ላይ በተፈፀመው የጌታ ሥራ የተከናወነ በመሆኑ በዘመናት ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ የሚፈልጉ ኢአማንያን ሌላ መሥዋዕት ሳያስፈልጋቸው በመስቀሉ ሥራ ይታረቃሉ::

በየዘመናቱ የሚፈጸም የማስታረቅ ሥራ ባይኖርም የማስታረቅ አገልግሎት አለ:: ይህም በወንጌል ስብከት በኩል የሚፈፀም የማስታረቅ አገልግሎት ነው:: በመስቀል ላይ በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ የነበረው ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ሁሉ የማስታረቅ አገልግሎቱንም ለክርስቶስ መልእክተኞች የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ነው፤ ይህንንም ሐዋርያው ሲገልጥ «ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰ

*(ወደ ገጽ 9 ይዞራል)*

## ከፈሪሳውያን እርሾ.. ከገጽ4 የዞረ

ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ፤ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል» ሲል አስተምሮአል/ማቴ6፡5-6/:: እዚህ ላይ ይህ ለምጽዋትና ለጸሎት ተባለ እንጂ በግል የምናደርገው ነገር ሁሉ ይህንኑ መርህ የተከተለ ሊሆን ይገባል:: በሰው ዓይን በመታየት ከሰው ምስጋናና ጥቅምን ለማግኘት የሚደረግ ማናቸውም መንፈሳዊ ሥራ ትርፉ ያው ከሰው ብቻ የሚገኝ ነገር ነው:: የምናደርገውን ነገር ሁሉ ለጌታ ካለን ፍቅር የተነሳ ብቻ ልናደርግና ይህንንም ከግብዝነት በራቀ መንገድ ልንፈጽመው ይጠበቅብናል:: ምናልባትም ሰዎች አሁን ስለሚያደርጉት ነገር «ይህን የምናደርገው በግብዝነት አይደለም» ሊሉ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ልብን ወደሚያውቅ ጌታ በቤት ውስጥ የሚጸልይ በጸሎት ጩኸት ጎረቤቱን ቢያውክ፣ የሚያደርገውን በስውር ማድረግ ሲችል ሆን ብሎ በሰው ፊት ቢያደረግ፣ ያ ሰው የሚያደርገውን «ግብዝነት አይደለም» ከሚል ይልቅ «ግብዝ መሆኔን አላውቅም» ቢል ይቀለዋል:: ጌታ እንደዚሁም «ስትጦሙም እንደግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል፤ አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ፤ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል» ይለናል /ማቴ6፡16-18/:: እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ የጌታ ትምህርቶችን አንብበን በአንጻሩ ሰዎች ይህንኑ ጌታ አታድርጉት ያለውን ሲያደርጉ ስናይና ይህም ስህተት ነው ተብሎ ከመጠርጠር አልፎ እንደመደበኛ የክርስቲያን አካሄድ፣ የሃይማኖተኞችም የጨዋነታቸው መታወቂያ ተደርጎ ሲሠራበት ስንመለከት፣ በእርግጥ እርሾው ሊጡን ሁሉ እንዳቦካ ቅንጣት ያህል አያጠራጥርም:: ብዙዎች በፈሪሳውያን የግብዝነት ምጽዋት፣ ጸሎትና ጾም እንዲገለጡ በሚበረታቱበትና በዚሁ ግብዝነትም ተገልጠው በሚገኙበት በዚህ ዘመን በእርሾው ላልተለወሱት አማኞች ጌታ አሁንም በሉ በኩል «ተጠንቀቁና ተጠበቁ» ይላል::

### አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ፤ ዘርፋን ያስረዝማሉ/ቁ.5/

ይህ ደግሞ በአላባበስ ራሱን መንፈሳዊ አድርጎ ለመግለጥ የሚፈልግ የፈሪሳውያን የግብዝነት እርሾ ነው:: አሸንክታብ ማለት በዘጸአትና በዘዳግም መጻሕፍት የተነገረውን በፊደል በመከተል የተገኘ በአካል ላይ የሚንጠለጠል «ጥፈት» ወይም «ክታብ» ነው:: በአገራችን «ጥፈት» ወይም «ክታብ» ከሚባለው የሚለየው በዚህኛው በብራናው ላይ የሚጻፈው ራሱ በዘጸ13፡9-10 ያለውና በዘዳ6፡9 ያለው ቃል ነው፤ ጥፈቱም በእብራይስጥ ቴፍሊን ይባላል:: ከሁለቱ ጥቅሶች ውስጥ አንደኛው ጥቅስ በብራና ተጽፎ በግንባር ላይ የሚታሰር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በግራ እጅ ክንድ ላይ ይታሰራል:: በሁለቱም ጥቅሶች ላይ «በእጅህ ምልክት አድርገህ እሰረው፤ በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ» የሚለው ትእዛዝ ለዚህ አድራጎት እንደመነሻ ያገለገለ ሲሆን አይሁድ በዚህ ላይ ከዚህም ያለፈ አመለካከት አላቸው፤ ቤራኮት የሚባለው የታልሙድ ክፍል ስለዚህ ጥቅም ሲናገር ይህን አሸንክታብ በቤትም ሆነ በውጭ አስሮ መሄድ በሌሊትም እንኳን አጋንንት ያባርራል ይላል:: በዚህ መልኩ አይሁድ መንፈሱን ስተው በፊደሉ በመሄድ ራሳቸው የሚጽፉትን ብራና ወደመታመን ገቡ:: ፈሪሳውያን በዚህ ጉዳይ ከሌላው ሕዝብ የሚለያቸው ደግሞ ይህንኑ አሸንክታብ ከሚገባው በላይ ሰፊ በሆነ ብራና ላይ ጽፈው ክታቡን በማተለቅ በዚህ ጽድቻቸውን ለመግለጥ መጣራቸው ነው::

ከዚህም ሌላ የሚለብሱትን ልብስ ዘርፍ ከመጠን በላይ በማስረዘም በዚያም በዘኁ15፡38 እያንዳንዱ እስራኤላዊ

*(ወደ ገጽ 9 ይዞራል)*

## የማስታረቅ....ከገጽ 8 የዞረ

ጠን ከእግዚአብሔር ነው» ብሏል /2ቆሮ5:18/፤ ተበዳዩ ራሱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ በጠላትነት ላሉት ኢአማንያን የሚሆን የማስታረቅ አገልግሎትን መስጠት እንዴት የሚደንቅ ፍቅር ነው! እንደምንስ ያለ ድንቅ ምሕረት ነው! ከዚህ ፍቅርና ምሕረት ጋር የሚመሳሰል ምሕረትና ፍቅር ከወዴት ይገኛል? እርቁን ሊፈልጉ የሚገባቸው የእግዚአብሔር ቁጣና ዘላለማዊ ፍርድ በእነርሱ ላይ ያለባቸው ኢአማንያን ራሳቸው መሆን ሲገባቸው ስለእነርሱ በማሰብ የማስታረቅን አገልግሎት የሚሰጣቸው ይህ አምላክ ምን ዓይነት የፍቅር አምላክ ነው? እንዴትስ ያለ አዛኝ ልብ አለው? አገልጋዮችስ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም የተከፈለበትን ይህንን የማስታረቅ አገልግሎት ምን ያህል አስተውለውትና ተረድተውት ይሆን? አይሁድ ምልክትን ሲለምኑ የግሪክ ሰዎች ደግሞ ጥበብን ሲፈልጉ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን የምንሰብክበት ምክንያት ሰዎች በሚመጣው የእግዚአ ብሔር ቁጣና ዘላለማዊ ፍርድ ከመጥፋታቸው በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ከወዲሁ እንዲታረቁ ለማድረግ መሆኑን ሊያውቁ ይገባቸዋል::

እግዚአብሔርን የማያመልክ ዓለም ራሱን ለጥፋት እያዘጋጀ ባለበት በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በማስታረቅ ል የተሞሉ አገልጋዮች ምንኛ ያስፈልጋሉ! ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ በሐዋርያነቱ የእግዚአብሔርን ል ለሕ ዝቡ በማቅረብ ሕዝቡ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እየመጣ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅ ይለምን ነበር:: በእርሱም ስፍራ ሆነው ይህንንው የማስታረቅ አገልግሎትን ያገለግሉ የነበሩት ሐዋርያት ለማያምነው ዓለም በፍቅር የማስታረቅን ል ሲያቀርቡ አይታክቱም ነበር፤ በማታረቅም ል የተሞሉ ነበሩ፤ ስለዚህም ሐዋርያው በእኛም የማስታረቅን ል አኖረ» ሲ ል ችሏል/2ቆሮ5:19/:: በአንዳንድ ስፍራ በእንባ ጭምር ለሕዝቡ የእግዚ አብሔርን ል በማቅረብ ጌታ የሰጣቸውን የማስታረቅ አገልግሎት ያገለግሉ ነበር/የሐዋ.ሥራ20:31/፤ እየለመኑም ጭምር ያገለግሉ ነበር /ሮሜ12:1/፤ ከዚህ ጋር ሲተያይ በዚህ ዘመን ያለን አገልጋዮች ስልቹነትና ትዕግሥት የለሽነት የማስታረቅ አገልግሎትን የሚፈን ሆኖ እናገኘዋለን:: አንዳንዶቻችን ደግሞ ከእግዚአ ብሔር ጋር ያልታረቁ ሰዎች ጉዳይ በጣም እያሳሰበን ለዚሁ የማስታረቅ አገልግሎት መትጋታችን አልቀረም:: ለዚህም የማስታረቅ አገልግሎት የሚሆን ድርጅት እናቋቁማለን፤ ፈንድ /ገንዘብም/ እናሰባስባለን፤ የተለያዩ የወንጌል ሥርጭት ዘዴዎችንም እንቀይሳለን፤ በጣም የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቻችን ይህን ሁሉ ይዘን ሳለ የማስታረቅ ልን ግን አልያዝንም፤ እግዚአብሔር ሲመለከተን ምን ይል ይሆን? በማስታረቅ አገልግሎት ስም ብዙ እንቅስቃሴዎችን አድርገን ሳለ ራ ሳችንን አስተዋውቀንና ዝነኞች ከሆንን በኋላ ለኢአማንያኑ ሕዝብ ግን የማስታረቅን ል ማቅረብ አለመቻላችን ምን ያህል ያሳዝነው ይሆን? በዚህ ዓይነት ሆኔታ ውስጥ የምንገኝ አገልጋዮች ጥቂት ቆም ብለን ንስሐ ልንገባ ያስፈልገናል:: ከላይ የተዘረዘሩት የተሚሉ ሁኔታዎች ባይኖሩንም፣ ምስኪኖችና ብዙም ታዋቂነት የሌላቸው ብንሆንም የማስታረቅ ል ካለን ጌታ የሰጠንን የማስታረቅ አገልግሎት

*(ወደ ገጽ 18 ይዞራል)*

## ከፈሪሳውያን እርሾ...ከገጽ 8 የዞረ

በልብሱ ላይ ዘርፍ ያድርግ የተባለውን ከሌላው በተሻለ መልክ እያደረጉት መሆኑን ለማሳየት ይሞክሩ ነበር:: ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በሕይወታቸው በመተግበር እንጂ ሉን ጽፈው በሰውነታቸው ላይ በማንጠልጠል እግዚአ ብሔርን ደስ ሊያሰኙት እንደማይችሉ ሊያውቁት በተገባቸው ነበር፤ ሉን ሰምቶ ማድረግ የሉን ባለቤት ደስ ያሰኛል፤ እነርሱ ግን ሉን ጽፈው በአካላቸው ላይ በማንጠልጠል ከዚያውም አሸንክታቡን በማስፋት ግብዝነታቸውን ይገልጡ ነበር:: በመሆኑም በአሸንክታባቸው ስፋትና በልብሳቸው የዘርፍ ርዝመት ከሌላው ሕዝብ ተለይተው ይታዩ ነበር::

ማንኛውም ክርስቲያን በአግባቡ እንዲለብስ በዚህም ከማያምነው እንዲለይ የሚያሳስቡ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች ቢኖሩም/1ቆሮ11:4-16፣ 1ጢሞ2:10/፣ አማኙን ከአማኙ የሚለይ፣ ትጋትን ወይም የአገልግሎትን ድርሻ ለማሳየት የሚውል፣ በሕዝብ መካከል ለባሹን «እገሌ» የሚያሰኝ ልብስ በቤተክርስቲያን አልነበረም፤ ይሁን እንጂ ከፈሪሳውያን እርሾ ባልተጠበቁ አማኞች መካከል የተለየ ወገንን የሚያሳዩ አለባበሶች መታየት የጀመሩት ጌታ ይህን ትምህርት ካስተማረ ብዙ ምእተ ዓመታት ሳይቆጠር ነው:: እምነትም ሆነ ማናቸውም መንፈሳዊ ተግባር በውስጥ ሰውነትና በሥራ መገለጥ ሲኖርበት በአፍአዊ ልብስ ወደ መገለጥ መሄዱ የሰው ልጅ ልብ ምን ያህል ለፈሪሳውያን ግብዝነት የተመቸ እንደሆነ ያሳያል፤ ይኸው ዝንባሌ እያደገ መጥቶ ልብሰ-ተክህኖ፣ ልብሰ-መዘምራን፣ ልብሰ -ጵጵስና፣ ልብሰ-ምንኩስና ወዘተ እየተባለ የሚሠራበት አፍአዊ ማንነትን የሚገልጥ ልብስ የቤተክርስቲያንን ትክክለኛ ጠባይ በለቀቀ ሁሉ ዘንድ የሚዘወተር ሆነ:: ዛሬም ሳይቀር እነዚህ አልባሳት የአዲስ ኪዳን ትምህርት አንዳችም መነሻ ሳይኖራቸው ሥልጣኔ ባስገኛቸው በብዙ ውድ ነገሮች ከተዋቡ በኋላ በእግዚአብሔር ል የተከለከለውን ግብዝነት እንዲገልጡ ሲደረግ ይታያል::

በሌላ በኩልም ጌታ በመስቀሉ መከራ ስለስሙ ፍቅር ስንል እንድንካፈል እንጂ የተመሳቀለ ቅርጽ አሠርተን በአንገታችን እንድናንጠለጥል አላስተማረንም ነበር፤ ከመከራው የምንካፈልበትን እምነት ብንይዝም እንኳ ለዚህ የሚሆን የተመሳቀለ ቅርጻ ቅርጽ ማሠራቱ ከግብዝነት ያለፈ አይደለም፤ የሚገርመው ግን ይኸው ግብዝነት እናምናለን ከሚሉት አልፎ ዓለማዊነት በልባቸው በነገሠባቸው ሰዎች አንገትና ደረት ላይ ጭምር ከብርና ከወርቅ በሚሠሩ በተመሳቀሉ ቅርጻ ቅርጾች ተገልጦ መታየቱ ነው:: ይህም ሊገልጠው የሚችለው ክርስትናን ሳይሆን ግብዝነትን ብቻ ነው::

በአጠቃይ በአልባሳትና በሰው ሰራሽ ቅርጻቅርጽ ራሱን ለመግለጥ የሚፈልግ ሰውም ሆነ ሥርዓት በእርግጥ በግብዝነት እርሾ ተወስዷል:: ከዚህ እርሾ በተጠበቁት እውነተኛ አማኞች ግን የሚታየው በውስጥ ሰውነት የሚኖርና በሥራ የሚገለጥ ሕይወት ነው::

### በምሳ የከበሬታ ስፍራ፣

### በምኩራብ የከበሬታ ወንበር /ቁ.፮/

ሌላው የፈሪሳውያን ጠባይ ከበሬታን በአደባባይ መፈለጋቸው ነው:: ከሰው የተለየ ከበሬታ እንዲሰጣቸው ተለይተው እንዲታወቁ ራሳቸውን በአለባበስ የለዩ በመሆናቸው በማናቸውም ጊዜና ቦታ ያያቸው ሁሉ ከልብሳቸው የተነሳ ያከብራቸዋል፤ ይህም ከሚፈጸምባቸው ስፍራዎች አንዱ የግብዣ ስፍራ ሲሆን ሌላው ደግሞ ምኩራብ ነው:: ሰዎች በምሳ የሚቀመጡበት ስፍራ የተቀማጩን ማንነትና ክብር እንዲገልጥ ታስቦ የሚዘጋጅ በመሆኑ ፈሪሳውያን በዚያ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛሉ:: በምኩራብም ቢሆን ከሕዝቡ ጋር የሚቀመጡ ሳይሆኑ ከሕዝቡ የተለየ ወንበር ያላቸው ነበሩ፤ በቤተመቅደስም ቢሆን አቀማመጣቸው ይህንኑ ይከተላል፤ ሕዝቡ ፊቱን ወደ መቅደሱ አዙሮ ሲቀመጥ እነርሱ ደግሞ ፊታቸውን ወደ ሕዝቡ ጀርባቸውን ወደ መቅደሱ አድርገው ይቀመጣሉ::

በዚህ ጉዳይም ቢሆን እርሾው እንደምን ዛሬ በምድር ላይ ያሉ «ሃይማኖተኞችን» እንደወረሰ ለማየት ሩቅ መሄድ አያስፈልግም:: አገልጋዮች የሚባሉት በግብዣ ስፍራ የተለየ ወንበር አላቸው፤ በአምልኮ ስፍራም ለእነርሱ «ተይዟል» የሚል ወረቀት የተለጠፈባቸው ወንበሮች

*(ወደ ገጽ 10 ይዞራል)*

**ከፈሪሳውያን እርሾ**..ከገጽ 9 የዞረ

ወይም ደግሞ ፊታቸውን ወደ ሕዝብ አዙረው እንዲቀመጡ የሚያስችላቸው ወንበር ከአበባ ጋር ይዘጋጅላቸዋል፤ አንዳንዶች ደግሞ ከዚህም አልፈው የነገሥታትን ዙፋናት የሚመስሉና ከእነርሱ በቀር ሌላ የማይቀመጥባቸው የሚያብረቀርቁ መናብርት አሏቸው:: በመቀመጫቸው ክብራቸውን ለመግለጥ ይወዳሉ፤ በመንገድ እንኳን ሲሄዱ ተራ «ምእመን» ከሚሉት ሕዝብ ተቀይጠው የማይሄዱ፣ ክብር ከሚሆን ስፍራ ካልሆነ ከሌላ መድረስ እንደውርደት ወይም እንደአለመባረክ የሚቆጥሩ ምንኛ ብዙ ናቸው! ከዚህ ለመውጣት ለሚሹና የጌታን ትምህርት ለሚከተሉ መፍትሔው አሁንም «እርሾውን» ማስወገድ ነው::

## በገበያ ሰላምታ ይወዳሉ/ቁ.7/

በእርግጥ ከላይ የተዘረዘሩትም ሆኑ ይህ በዚህ ንዑስ ርእስ የተገለጠው ፍላጎት የአሮጌው ሰውነት፣ ያልተለወጠ አዳማዊ ባሕርይ ነው:: በገበያ ሰላምታን ለመቀበል መውደድ በራሱ በዚያ አደባባይም እንኳን ክብርን መፈለግ እንደሆነ ግልጥ ነው:: ፈሪሳውያን በገበያ መካከል ሰው ወደ እነርሱ እየቀረበ ሰላምታን ሲሰጣቸው የሌላውን ትኩረት እንዳገኙ ይሰማቸዋል፤ ይህንን ትኩረት ሲያጡ ደግሞ ከሌላው ይለየናል የሚሉት «ጽድቻው» ዋጋ እንዳጣ ይሰማቸዋል::

ለሚያምን ሰው የአምላኩን ትኩረት ማግኘቱ በቂው ነው፤ ልብ በፈሪሳውያን እርሾ ሲበከል ግን የሰው ፍላጎት በዚህ የሚረካ አይደለም፤ ከዚህም የተነሳ ሌሎች ስለ እርሱ ያላቸውን አክብሮት በአደባባይ እንዲገልጡለት ይፈልጋል:: እንደ ገበያ ባሉ ሕዝብ ሰብሰብ ባለባቸው ስፍራዎች ሁሉ መካከል ላይ ቆመው የብዙዎችን ሰላምታ የሚናፍቁ፣ ሰው ሁሉ ሰላምታ ሲሰጣቸው ደስ የሚሰኙ፣ ወይም ሁሉም መጥቶ እጃቸውን እንዲሳለማቸው የሚፈልጉ፣ አሊያም በክብር ቦታቸው ቆም ብለው የሚጨብጣቸውን የሚጠብቁ ግብዞች በሞሉባት ዓለም ላይ እንገኛለን::

የክርስቶስ ሰላም ያላቸው ግን እነርሱ ሄደው ሌላውን ሁሉ ሳያበላልጡና ሳይዘነጉ ሰላምታ መስጠትን እንጂ ሰው መጥቶ ሰላምታ እንዲሰጣቸው አይናፍቁም፤ ለሌላው ሰው ትኩረት መስጠታቸውን እንጂ ሰው ለእነርሱ ትኩረት እንዲቸራቸው አይጠብቁም:: በመሆኑ ከዚህ የገበያ ሰላምታን ከሚፈልግ ግብዝነት መለየት ከፈሪሳውያን እርሾ መጠበቅ ነው::

## መምህር ሆይ መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ /ቁ.7/

ግብዝነት የገበያ ሰላምታን በመውደድ ብቻ አያበቃም፤ ሃይማኖታዊ የማዕርግ መጠሪያዎችንም በመውሰድ በዚያ ማንነቱን ይገልጣል፤ ከእነዚህም መጠሪያዎች በዚህ ክፍል የተጠቀሱት መምህር፣ አባት እና ሊቅ የሚሉት ናቸው:: ሰዎች በዚህ እርሾ ተጽዕኖ ሥር ሲወድቁ የእነዚህ መጠሪያ ቅጽሎችና የሌሎችም ተጠሪ ለመሆን ያላቸው መሻት ከምንጊዜውም በላይ እየጨመረ ይሄዳል:: ጌታ ግን ይሰሙት ለነበሩት ህዝብና ለደቀመዛሙርቱ «እናንተ ግን መምህር ተብላችሁ አትጠሩ»/ቁ.8/፣ «በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ»/ቁ.9/፣ «ሊውንት ተብላችሁ አትጠሩ»/ቁ.10/ እያለ አስተማረ:: ምንም እንኳን በክርስቶስ ትምህርት የጠነከሩና ከጌታ ጋር ባላቸው ነገር የበሰሉ ከመሆናቸው የተነሣ እንደ አባት ሊታዩ የሚችሉ ሰዎች በመካከላችን ቢኖሩም እነርሱን «አባት» ብሎ መጥራት ግን ተገቢ አይደለም፤ በዚህ መጠራቱም ቢሆን ግብዝነት ነው::

ጌታ «መምህራችሁ አንድ ስለሆነ መምህር ተብላችሁ አትጠሩ» በማለት ያስተማረን ትምህርትም ሊስተዋል ይገባል፤ ምንም እንኳን «አስተማሪነት» አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ቢሆንም /ኤፌ4:11፤ 1ቆሮ12:28-29፤ ሮሜ12:7/ በአስተማሪነት በማገልገልና «መምህር» የሚል ቅጽል በስም ላይ ደርቦ መጠሪያ በማድረግ መካከል ታላቅ ልዩነት መኖሩ ሊታወቅ ይገባል:: በኤፌ4:11 የተዘረዘሩትን የጸጋ ስጦታዎችንም ሆነ ሌሎችን መጠሪያ አድርጎ በዚያ መጠራት ወይም ስምን ማስዋብ ያለጥርጥር የፈሪሳውያን ግብዝነት ነው፤ ጳውሎስም ሆነ ሌሎች የጌታ ሐዋርያት የሐዋርያነት ጸጋ እንደተሰጣቸው የሚጠራጠር የለም፤ እነርሱም በውል ያውቁታል፤ ሆኖም ግን በሕይወት ዘመናቸው እርስ በርሳቸው ሲጠራሩ «ሐዋርያው ጴጥሮስ»፣ «ሐዋርያው ዮሐንስ» ተባብለው አያውቁም፤ በምትኩ ግን ጴጥሮስ ጳውሎስን ሲያነሳው «የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ» ብሎ እንደጠራው እናነባለን/2ጴጥ3:15/:: ይህም ጌታ «እናንተ ግን............. ተብላችሁ አትጠሩ»፤ «እናንተ ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ»/ቁ.8/ ብሎ ያስተማረውን መከተላቸውን ያሳያል::

መምህር፣ መሪጌታ፣ ቀኛጌታ፣ አባ፣ አቡነ፣ ቄስ፣ ዲያቆን ከሚሉት ነጠላ ቅጽሎች አንስቶ ሊቀሊውንት፣ ሊቀ ትጉኃን፣ ብፁዕ ወቅዱስ፣ ርእሰ ርኡሳን፣ መልአከ-ሕይወት፣ መልአከ-ፀሐይ፣ መልአከ-ኃይል፣ እስከሚሉት ተደራራቢ ማዕርጋት ድረስ ያሉትም ሆኑ እንዲሁ እጩ ወንጌላዊ፣ ወንጌላዊ፣ ምክትል ፓስተር፣ ፓስተር፣ ሲኒየር ፓስተር ከሚሉት አንስቶ «የእግዚአብሔር ሰው»፣ ዛሬ ዛሬ ደግሞ «ሐዋርያው» እስከሚሉት ድረስ ያሉት ሁሉ ያለመለየት የግብዝነት መገለጫዎች ናቸው፤ ከሁሉም ከሁሉም የሚደንቀው ደግሞ በላቲን <u>ፓስተር</u> ማለት በአማርኛ <u>እረኛ</u> ማለት ሆኖ ሳለ ፓስተር የሚለው የላቲን ቃል ለአንዳንዶች እንደማዕርግ ስም ሆኖ እንዲያገለግል መደረጉና እረኛ የሚለው ቃል ደግሞ እንደሌላ የአገልግሎት ዘርፍ መታየቱ ነው፤ በአንድ ጉባኤ ውስጥ ፓስተሮችም፣ እረኞችም እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች መኖራቸው፣ በተለይም ፓስተር የሚለውን ቃል ለሚበልጥ ማዕርግ መጠቀምና እረኛነትን ላነሰ አገልግሎት መግለጫ አድርጎ መገልገል ቋንቋን አለማወቅ ከመሆኑም በላይ የሰው ልብ ምን ያህል በእርሾው እንደ ጠፋ ያሳያል:: መጋቢ የሚለው ቃልም ቢሆን ፓስተር ለሚለው የላቲን ቃል ትርጉም ካለመሆኑም ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከጸጋ ስጦታዎች እንደ አንዱ ለብቻው የሚታይ አይደለም፤ የማዕርግ መጠሪያም አይደለም፤ ማናቸውም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማህበርን ለማነጽ እስከተሰጠ ድረስ ያ የተሰጠው ሰው የመጋቢነት አገልግሎት አለው፤ ሐዋርያትም እንኳ መጋቢዎች ነበሩ/1ቆሮ4:1/፤ ይሁን እንጂ መጋቢ የሚል ቅጽልን በስም ላይ መደረቱ ለየት ያለ ፍላጎት ነው:: የእረኛነት ጸጋ የተሰጠው ስሙ «እገሌ» የሆነ ሰው ስለአገልግሎቱ ዓይነት ቢጠየቅ እረኛነት/ፓስተርነት-ኖላዊነት/ ነው ሊል ይችላል፤ ሌሎችም ስለ እርሱ ቢጠየቁ በእረኛነት እንደሚያገለግል ሊናገሩ ይችላሉ፤ እርሱን ሲጠሩት ግን በጌታ ወንድማቸው ነውና ወንድም «እገሌ» ማለት በቂና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፤ እርሱም በሥራ ቦታው ወይም በሌላ ስፍራ በእምነት ወንድሞቹ ባልሆኑት መካከል ስለማንነቱ ቢጠየቅ እንደተወለደበት ባህል አቶ «እግሌ» ወይም ሚስተር «ሶ ኤንድ ሶ» ይላል እንጂ ፓስተር «እገሌ» አይልም:: የመታወቂያ ደብተሩም አቶ «እገሌ» ይላል እንጂ ፓስተር «እገሌ» አይልም፤ ስለሥራው ቢጠየቅ ግን ሥራዬ እረኛነት ነው ማለት ይችላል:: እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳለ እራሱን «የሰው ልጅ» እያለ የጠራውን ጌታ የሚከተሉ ያለጥርጥር ከፈሪሳውያን የማዕርጋት እርሾ ተለይተው በሚያምኑት ዘንድ «ወንድም» ተብለው በመጠራት ደስ እየተሰኙ ይኖራሉ፤ እነርሱም በዚህ ምድር በማያምኑት ዘንድ «የነቀፌታ» ስፍራን/ዕብ13:13/ ቢይዙም በጌታ ዘንድ ግን «በሰማያዊ ስፍራ»/ኤፌ2:7/ መቀመጣቸውን በማወቅ ልባቸውን ከፈሪሳውያን ግብዝነት ይጠብቃሉ::

**«ለእውነት እየታዘዛችሁ <u>ግብዝነት ለሌለበት</u> ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን እንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ»**/1ጴጥ1:22/::

**ጌታ ቢፈቅድ ይቀጥላል::**

**የአዲስ ኪዳን**. .. ከገጽ 7 የዞረ

ተለይተው የካህናት ወገን ይሆኑ ነበር:: ከእነርሱ ውጪ የሆነ ሌላ ሰው በክህነት ሊያገለግል አይችልም ነበር /ዘኁ16:40፣ 18:5/:: በየዕለቱም ሆነ በየሳምንቱ የሚፈጸመውን ሥርዓተ አምልኮ የሚመሩ ካህናት በተራ ወይም በሰሞን ይመደቡ ነበር:: በተለይም በዳዊት ዘመን በዕጣ ተመድበው የሚያገለግሉ 24 ካህናት ነበሩ/2ዜና24:1-19/፤ ይህም በተራ እየተመደቡ በክህነት ማገልገል ጌታችን እስከ ተወለደበት ዘመን ድረስ እንደቀጠለ ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ይቻላል፤ በሉ1:8-10 ዘካርያስ በክፍሉ ተራ መሠረት በመቅደስ ገብቶ ያገለግል እንደነበርና ሕዝቡ ግን በውጭ ቆመው ይጸልዩ እንደ ነበር እናነባለን፤ ስለሆነም የብሉይ ኪዳን አምልኮ በዚህ ዓይነት ካህናቱ በመቅደስ ውስጥ ሕዝቡ ግን በውጪ ሆኖ የሚፈፀም አምልኮ ነበር::

በአዲስ ኪዳን ግን ከዚህ በተለየ መልኩ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ካህናት እንደሆኑ በግልጽ ተጽፎልናል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሲገልጥ «..... በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኛ <u>መንፈሳዊ መሥዋዕትን</u> ታቀርቡ ዘንድ <u>ቅዱሳን ካህናት</u> እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ» ይላል/1ጴጥ2:5/፤ በዚህ ቃል ውስጥ ከአምልኮ ጋር የተያያዘው የአማኞች ክህነት ተነግሮናል፤ በብሉይ ኪዳን የነበሩት ካህናት በሚመሩት አምልኮ ውስጥ ዋናው የአምልኮ ክፍል የእንስሳት መሥዋዕትን ማቅረብ ነበር:: በመሆኑም ካህናት ሕዝቡን ሁሉ በመወከል በመሠዊያው ላይ የተለያየ መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር፤ በአዲስ ኪዳን ግን ለእግዚአብሔር የሚቀርበው መሥዋዕት «መንፈሳዊ መሥዋዕት» ነው፤ ይህም መንፈሳዊ መሥዋዕት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በኤፌ5:2 ላይ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ራሱን ለእኛ አሳልፎ እንደሰጠ ተጽፏል፤ በዕብራውያን መልእክትም ጌታ ኢየሱስ ራሱን ዘላለማዊ መሥዋዕት አድርጎ እንዳቀረበ በተደጋጋሚ ተገልጧል/ዕብ7:27፤ 9:9-14እና26፣ 10:11-22/:: ስለዚህ በአዲስ ኪዳን አምልኮ ውስጥ ለእግዚአብሔር የምናቀርበውና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው መሥዋዕት ራሱን አንድ ጊዜ ለዘላለም ያቀረበው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ይህንንም የምናቀርበው በመንፈሳዊ መንገድና በእምነት ነው፤ ይህም ስለ ጌታ ኢየሱስ የሚናገሩና መሥዋዕትነቱን የሚያወሱ ቅዱሳን የምስጋና ቃላትን ወደ እግዚአብሔር በመናገርና እርሱን የሚመለከቱ ዝማሬዎችን በመዘመር ሊገለጥ ይችላል:: እንዲህ ያለውን የተወደደ አምልኮ ከምእመናን ተለይተው መሪ ሆነው የሚመደቡ ሰዎች ሊመሩት አይችሉም:: በመሠረቱ ሁላችንም ቅዱሳን ካህናት የሆንነው መንፈሳዊ መሥዋዕትን እናቀርብ ዘንድ ነው፤ ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ከምእመናን መካከል ተራም ሆነ ሰሞን ወይም ፕሮግራም ሊወጣለት የሚገባው የካህናት ቡድን የለም:: ሁላችንም ካህናት በመሆናችን በአንድነት በሰማያዊት መቅደስ ገብተን መሥዋዕቱን የማቅረብ እኩል መብት አለን፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሁላችን በሞተ ጊዜ ካህናቱንና ሕዝቡን ይለይ የነበረው የቤተመቅደስ መጋረጃ ዳግም ላይዘጋ ለሁለት ተቀዷል /ማቴ27:51/፤ ይህም በሰው እጅ ወዳልተሠራችው ቅድስት እንገባ ዘንድ ለሁላችንም በሩ ክፍት መሆኑን ያሳየናል:: በመሆኑም የዕብራውያን ጸሐፊ እንዳለው ጌታ ኢየሱስ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት አለን/ዕብ10:19/:: በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ወደፊቱ እንገባ ዘንድ የሰጠን መጋረጃ የኢየሱስን ሥጋ ነው፤ በእርሱ በኩል ገብተን ወደ ዙፋኑ የመቅረብ ድፍረቱ አለን፤ ስለሆነም በዚህ ዘመን አንዳንድ የአምልኮ መሪዎች ከመጋረጃው ኋላ፣ ሕዝቡ ደግሞ ከመጋረጃው በስተውጭ ሆኖ የሚካሄደው አምልኮ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚያስችለው ይህ ድፍረት የሌለውና ሁሉም ካህናት ያልሆኑበትን አምልኮተ ኦሪት የተከተለ ነው:: ሁላችንንም ከነገድ ከቋንቋ ዋጅቶ ካህናት እንድንሆን ያደረገን ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው/ራእ1:6፤5:9-10/፤ ጴጥሮስ የሁላችንንም ካህናትነት ሲገልጥ «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ <u>የንጉሥ ካህናት</u> ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» ብሏል/1ጴጥ2:9/፤ ስለዚህ ሁላችንም ካህናት ከመሆናችን የተነሳ በምድር ላይ በአምልኮ ጊዜ እኛን የሚመሩ የተለዩ ካህናት ሊኖሩን አይገባም::

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን መጋረጃ ባይኖርም የስብሰባን መንገድ በመከተል ለአምልኮ ጉባኤ መሪዎችን መመደብም የአዲስ ኪዳን የአምልኮ ባሕርይ አይደለም፤ አንድ ግለሰብ አስመላኪ፣ ሕዝቡ ደግሞ አምላኪ የሚሆንበት ሥርዓትም አንዱ መሪ ህዝቡ ተመሪ ከሚሆንበት የዓለም ስብሰባ የተቀዳ ከመሆኑም ባሻገር በይዘቱም ከአምልኮተ ኦሪት ያልራቀ ነው:: ከሁሉም በፊት የአዲስ ኪዳን አምልኮ ጉባኤ ከሌሎች ጉባኤያት ወይም ስብሰባዎች በእጅጉ የተለየ መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፤ በአምልኮ ጉባኤ ተሰብሳቢዎች የሚያቀርቡት የራሳቸው የሆነ ሐሳብ የለም፤ የሚያደርጉትም ሁሉ እነርሱን ያማከለ ሳይሆን እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ ነው፤ የስብሰባውም መሪ ሰው ሳይሆን የሰውን ልብና የእግዚአብሔርንም መሻት የሚያውቀው መለኮታዊ አካል ነው::

ሁለት ወይም ሦስት ከዚያም በላይ ሆነን እግዚአብሔርን ልናመልክ ስንሰበሰብ በቀጥታ ጌታ ኢየሱስ ወደ ሚገኛበት ሰማያዊ መቅደስ በመንፈስ እንገባለን:: በዚያም ሊቀካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ የካህናቱን አምልኮ ይመራል፤ ጌታ ኢየሱስ ብቸኛ ሊቀካህናት ሲሆን ሁሉም የተሰበሰቡት ያለመለየት ካህናት ናቸው፤ አምልኮውም አማኞች በሙሉ እንደአሮን ልጆች ሆነው በጌታ ዙሪያ ተሰብስበው ጌታ ደግሞ በመካከላቸው እንደአሮን ሆኖ እየመራ የሚፈጸም የመንፈስ አገልግሎት ነው፤ በዚህ ረገድ ከሆነ ዛሬ ዛሬ አስመላኪ የሚባሉት ሰዎችም ሆኑ ሠራኢ ቄሶች የሚባሉት ራሳቸው በሊቀካህናችን በኢየሱስ የሚመሩ አምላኪዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል:: ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ያለችውን ጉባኤውን የሚመራው ደግሞ እርሱን ተክቶ አሁን በአማኞች ውስጥና በመካከላቸው በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው፤ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ የሚፈልገውን ነገር ይናገርበት ዘንድ በወደደው ሰው በኩል የምስጋና ቃል ወይም የምስጋና ዜማ ያመጣል፤ ሁላችንም ያን የምስጋና ቃል ወይም የምስጋና ዝማሬ ከተናገረው ወንድም ጋር በመተባበር በጋራ እናመልካለን:: በመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያንም ከጌታ እራት ጋር ተያይዞ ይካሄድ የነበረው የአምልኮ ጉባኤ አፈጻጸምም ይኸንኑ የተከተለ ነበር/ማቴ26:26-30፣ ሐዋ.ሥራ20:7፣ 1ቆሮ14:26/:: ጌታ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚመራውና የአካሉ ብልቶች ከሆኑ አማኞች የሚወጣው ይህ የአዲስ ኪዳን አምልኮ እግዚአብሔርን በእጅጉ ያስደስተዋል::

## የመዘምራን አገልግሎት መኖር

በሃይማኖተኛው የክርስትና ዓለም በስፋት እንደሚታየው የአምልኮ ጉባዔና የእግዚአብሔር ቃል የሚቀርብበት ጉባዔ ተለይተው አይታወቁም:: ሁለቱንም ባንድ ላይ የመቀላቀል ልማድ በስፋት ይታያል:: ከዚህም የተነሳ ሰባኪዎች በመድረክ ላይ ከመቆማቸው በፊትና ከጨረሱ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሕዝብ በማድረግ በመድረክ ላይ ተሰልፈው የሚዘምሩ መዘመራን መዝሙር ያቀርባሉ:: ይህም ሥርዓት እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት በሚያመልክ ጉባዔ ሊታይ አይገባውም::

በመጀመሪያ ደረጃ መዝሙር ወደ እግዚአብሔር የሚዜምና የከንፈር ፍሬ የሆነ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት መሆኑ ሊስተዋል ይገባል፤ «እንግዲህ ዘወትር <u>ለእግዚአብሔር</u> የምስጋናን መሥዋዕት ማለት

*(ወደ ገጽ 13 የዞረ)*

## የክርስቶስ አካል..ከገጽ 6 የዞረ

እንደሆኑ በመቁጠር ብዙ የዋሃን ከእነርሱ ጸጋን እንዲቀበሉ እየናፈቁና እያደረጉ ይሆን? አንባቢው ያስተውል:: የአማኟ ድርሻ ሉ በሚፈቅደው መንገድ ራስ ከሆነው ጌታ ጋር ያለው ግንኙት ጤናማ መሆን አለመሆኑን ማስተዋል ነው፤ ከዚህ በኋላ ይህንን አማኟ በአካሉ ውስጥ በጸጋ መግለጥ ራስ የሆነው የጌታ ሥራ ነው፤ እርሱም ይህን የሚሠራው በአካሉና በእያንዳንዱ ብልት በሚኖረው መንፈሱ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ይህንን እንደወደደ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል /1ቆሮ12፡13/::

## የብልቶች የእርስ በእርስ ግንኙነት

ብልቶች ሁሉ ተሰባስበው አካል እንደሚሠሩ ከላይ ተመልክተናል፤ አሁን ደግሞ እጅግ አስደናቂ የሆነውን የብልቶች የእርስ በእርስ ግንኙነት እንመለከታለን፤ ጳውሎስ በ1ቆሮ12፡25 ላይ «ነገር ግን ብልቶች እርስ በእርሳቸው በትክክል ይተሳሰቡ ዘንድ እንጂ በአካል መለያየት እንዳይሆን..... እግዚአብሔር አካልን አገጣጠመው» ይላል፤ ከዚህ ቃል ሐሳብ በቀላሉ ለመረዳት እንደሚቻለው እግዚአብሔር የሰውን አካል በሚሠራበት ጊዜ አካል የተገጣጠመ እንዲሆን ያደረገበት ዋናው ምክንያት በብልቶች መካከል መተሳሰብ እንዲኖርና መለያየት እንዳይኖር ነው:: እንዲሁ ይህ እውነታ ደግሞ ሕያዊት በሆነችው የክርስቶስ አካል ማለትም በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲሠራ ያስፈልጋል፤ ስለዚህ ሀዋርያው በሮሜ12፡4 ላይ «በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፤ እርስ በእርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን» በማለት እያንዳንዱ አማኟ ከሌላው አማኟ ጋር ያለውን የ ጠበቀ ግንኙነትና ኅብረት ያሳያል፤ የብልቶች መገጣጠም ያስፈለገበት ምክንያትም በአማኞች መካከል መተሳሳብ እንዲኖርና መለያየት እንዳይኖር ነው::

እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመነ ሰው ሌላውን አማኟ ለእርሱ እግዚአብሔር ያዘጋጀለት እውነተኛ ብልቱ እንደሆነ አድርጎ ሊቀበለው ይገባል:: ይህ በእያንዳንዱ አማኟ ሕይወት ተግባራዊ ሲሆን አንዱ አማኟ /ብልት/ ሲያዝን የሌላውም አማኟ ወይም ብልት ኀዘን ይሆናል፤ አንዱም ደስ ሲሰኛ ሌሎችም ከእርሱ ጋር ደስ ይሰኛሉ፤ በዚህም እውነተኛ የሆነው የብልቶች መተሳሰብና መሳሳብ ይገለጣል፤ ጌታም ሕያዊት በሆነች ቤተክርስቲያን ይህንን ማየት ይሻል::

**እነዚህን እውነታዎች መገንዘብ እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ይርዳን፤ አሜን::**

## እንነሣና... ከገጽ 1 የዞረ

ግን በኢየሩሳሌም ነበር:: ከወንድሞቹ አንዱ አናኒ እና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሌሎች ሰዎች ከይሁዳ አገር ከኢየሩሳሌም ከተማ ወደ እርሱ ወደ ሱሳ ግንብ በመጡ ጊዜ ወዲያውኑ ያነሣላቸው ጥያቄ ከምርኮ የተረፉትን አይሁድንና ከተማይቱን ኢየሩሳሌምን የሚመለከት ነበር/1፡1/፤ ይህም ነህምያ በልቡ ውስጥ የኢየሩሳሌም ነገር ሁል ጊዜም ይታሰበው እንደነበር ያሳያል፤ በተለይም «በዚያ ስፍራ ያሉት ከምርኮ የተረፉት ቅሬታዎች በታላቅ መከራና ስድብ አሉ፤ የኢየሩሳሌምም ቅጥር ፈርሷል፤ በሮችዋም በእሳት ተቃለዋል» የሚለውን ዜና ከእነሱ ሲሰማ ልቡም ሆነ ፊቱ ለአያሌ ቀናት በኀዘን እስኪሰበር ድረስ የኢየሩሳሌም ነገር በልቡ ውስጥ ተቀመጠ:: እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ያደርገው ዘንድ ያለውን ነገር በልቡ አኖሩለት /ነህ2፡12/፤ በዚህም ጉዳይ በሰማይ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት ይጾምና ይጸልይ ነበር/1፡4-11/፤ በጸሎቱም ውስጥ «ዛሬ ለባሪያህ አከናውንለት በዚህም ሰው ፊት ሞገስን ስጠው» ብሎ ከተናገረው ቃል እንደምንረዳው እግዚአብሔር በልቡ ያኖረለት የኢየሩሳሌም ነገር «ንጉሡን አስፈቅዶ በመሄድ የፈረሰውን ቅጥሯን ማደስ» እንደሆነ መረዳት ይቻላል፤ ቀጣዩ የነህምያ ታሪክም ይህንኑ ያስረዳል::

ታላቅ ለሆነ የእግዚአብሔር ሥራ በከፍተኛ መንፈሳዊ ቅንዓት/ቁጭት/ ለሚነሡ ሰዎች ነህምያ እንዴት ግሩም የሆነ አብነት ነው! የዚህ ዓለም ገዢ በሆነው በሰይጣን አሠራር ምክንያት ብዙ መንፈሳዊ ውድቀቶችን እየተመለከተ ልቡ የሚያዝን ሰው በልቡ ውስጥ እግዚአብሔር ያኖረለት ሥራ እንዳለ ከተሰማው በቅድሚያ በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ሊወድቅ እንደሚገባው ከነህምያ ይማራል:: ነህምያ በልቡ የኢየሩሳሌም ነገር ለአያሌ ቀናት ስላሳሰበው በራሱ መንገድና ዘዴ ከቤተመንግሥት ጠፍቶ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በሕገ-ወጥ መንገድ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሊሠራ አልፈለገም፤ ከዚያ ይልቅ በሕጋዊ መንገድ ሥራውን ይሠራ ዘንድ እግዚአብሔር በንጉሡ ፊት ሞገስን እንዲሰጠው በጾምና በጸሎት ለመነው፤ ከዚህም የተነሳ እግዚአብሐር በንጉሡ ፊት ሞገስ ስለሰጠው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቅጥሯን እንዲሠራ ፈድ ከማግኘቱም በተጨማሪ ለዚሁ መረጃ የሚሆን ደብዳቤም ተጻፈለት/ነህ2፡8-9/:: እግዚአብሔር ሥራውን ከሐቀኛና ሕጋዊ ከሆነው ባሕርዩ ጋር በሚጋጭ መንገድ ሊያሠራ አይፈልግም፤ አንዳንድ ጊዜ በራሳችን ምኞት በልባችን የሚፈጠሩትንና መሥራት የምንፈልጋቸውን ነገሮች ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበልናቸው ራእያት በመቁጠር ስንነሣ ሁል ጊዜም ሕገ-ወጥ መንገዶችን ለመጠቀም ወደ ኋላ አንልም፤ እግዚአብሔር በልቡ ያላኖረውን ሥራ ለመሥራት የተነሣ ሰው በድብቅ የሚሠሩ ሕገ-ወጥ መንገዶችን ለመገልገልም ልቡ ይደፍርለታል:: እንዲህ ያለውን የድብብቆሽ ሥራ ግን እግዚአብሔር በእጅጉ ይጸየፈዋል:: ስለሆነም በመጀመሪያ እግዚአብሔር በልባችን ያኖረውን ሥራ ለመሥራት መነሣታችንን ካረጋገጥን በኋላም ያንንም ሥራ በዚህች ምድር ላይ ለእግዚአብሔር እንድንሠራ እርሱ ራሱ የሰማይ አምላክ እንዲያከናውንልን በጾምና በጸሎት ሥራውን አሳልፈን ልንሰጠው ይገባናል::

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም በመኳዝ በብዙ መከራና ስድብ ለሚገኙት ወገኖቹ እግዚአብሔር በልቡ ያኖረለትን ሥራ ነገራቸው፤ «እኛ ያለንበትን ጉስቁልና ኢየሩሳሌም እንደፈረሰች በሮቿም በእሳት እንደተጠሉ ታያላችሁ፤ አሁንም ከእንግዲህ ወዲህ መሣለቂያ እንዳንሆን ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ» አላቸው፤ እነርሱም «እንነሣና እንሥራ» አሉ/ነህ2፡17-18/:: ከንጉሡ ፈድ እንዲያገኟ መከናወንን የሰጠው አምላክ በመከራና በስድብ እንዲሁም በታላቅ ጉስቁልና ያሉት የአይሁድ ቅሬታዎች «እንነሣና እንሥራ» ብለው ከእርሱ ጋር በሥራ እንዲተባበሩ በማድረግ የሥራውን ቅድመ ሁኔታ ሲያከናውንለት እናያለን:: እግዚአብሔር ሥራውን በልቡ ካኖረለት ሰው ጋር በመተባበር «እንነሣና እንሥራ» ማለት እንዴት ያለ ግሩም መታዘዝ ነው! እንዴትስ ያለ አስፈላጊ መነቃትና መነሣሣት ነው!

ነህምያ «ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ» የሚል ጥሪን ለሕዝብ ማቅረቡ ለአገልጋዮች መልካም ትምህርት ነው፤ ለብቻ የሚሠራ ምንም ነገር የለም፤ ሥራው እግዚአብሔር የሚከብርበት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከክፉ ሁሉ የሚጠበቅበት ሥራ እስከሆነ ድረስ ግለሰባዊ አይደለም፣ በማስተባበርና ወንጌልን በመስበክ አንዳንዶች ግንባር ቀደም ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ ለሁሉም ሕዝብ ኑና እንሥራ የሚል ጥሪ ሊያቀርቡ ይገባቸዋል:: ግለኛነትና እኔነት፣ የሥራውም ዋና ተጠሪ የመሆን ፍላጎት፣ እንዲሁም ዝነኛ ለመሆን የሚናፍቅ ስሜት እንደ ነህምያ ባሉ አገልጋዮች ዘንድ ቦታ የለውም፤ እንደ ነህምያ ያሉ

*(ወደ ገጽ 15 የዞረ)*

**ለእኛ ቀጥራችን እውነተኛውን አማኝ ከአፍ አማኙና ከከሃዲው ዓለም የሚለይ ከጌታና ከሐዋርያት የተቀበልነው ትምህርትና ክርስቲያናዊ የሆነው ምግባር ነው፤**

## የአዲስ ኪዳን.. ከገጽ 11 የዞረ

ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት» ተብሎ እንደተጻፈው የምስጋናው መሥዋዕት የሚቀርበው ለእግዚአብሔር ነው /ዕብ13፡15/፤ እንደዚሁም «በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ» በማለት መዝሙር ለእግዚአብሔር የሚዘመር መሆኑ በግልጽ ተነግሮናል /ቈላ3፡16/፤ ከዚህ አንጻር ህዝቡ ተቀምጦ መዘምራን ከመድረክ ወደ ሕዝብ መዝሙር ሲዘምሩ የሚደመጥበት ሥርዓት ከተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ጋር ምን ያህል እንደሚራን መረዳት ይቻላል:: በሕዝቡ ፈንታ መዘምራኑ እየዘመሩ ነው እንዳይባል የተለዩ ካህናት ስለሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርቡበት አገልግሎት አብቅቶ ሁሉም ካህናት ወደሆኑበት የአዲስ ኪዳን ዘመን ገብተናል::

ለመሆኑ የመዘምራን አገልግሎት የተቀዳው ከየት ነው? የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ስናጠና የዚህን ጥያቄ መልስ በቀላሉ መረዳት ይቻላል:: የመዘምራን አገልግሎት እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ አልነበረም፤ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት ከሴሎ ወደ ጽዮን ካመጣና ታቦቱም ዐርፎ ከተቀመጠ በኋላ በመገናኛው ድንኳን የሚያገለግሉ መዘምራንን አደራጀ/1ዜና6፡31-32/፤ መዘምራኑም ከሌዊ ነገድ ብቻ ነበሩ/1ዜና6፡48፤ 9፡33/፤ በአጠቃይ በዳዊት ዘመን 4ሺህ የሚሆኑ መዘምራን ነበሩ/1ዜና23፡5/፤ ከነዚህም ውስጥ ትንቢትም እየተናገሩ ያገለግሉ የነበሩት መዘመራን ቀጥር 288 ነበር/1ዜና25፡1-7/፤ አሳፍ፣ ኤማንና ኤዶታም በተባሉ አለቆች ለሦስት ተከፍለው ይመሩ ነበር፤ ለአገልግሎታቸውም ሰሞን/ተራ/ ነበራቸው/1ዜና25፡8-31/፤ ይህም ከዳዊትም በኋላ በየዘመናቱ ቀጥሏል:: ንጉሥ ሕዝቅያስ በዘመኑ ቤተመቅደሱን ከርኩሰት ካነፃ በኋላ መዘምራንን በማቆም ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ አድርጓል:: ስለዚህም የተጻፈው ቃል «ጉባኤም ሁሉ ሰገዱ፤ መዘምራኑም ዘመሩ፤ መለከተኞቹም ነፉ፤ የሚጠለው መሥዋዕት እስኪፈጸም ድረስ ሁሉ ይህ ሆነ» ይላል /2ዜና29፡28/:: በኢዮስያስ ዘመንም የመዘምራን አገልግሎት ነበር /2ዜና35፡15/፤ ከባቢሎን ምርኮ መልስም በእስራኤላውያን መካከል ከሌዋውያን ወገን የሆኑ 200 ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩ/ዕዝ2፡65/::

በአዲስ ኪዳን ግን ከምእመናን መካከል ተለይተው በሕዝብ ፊት ቆመው የሚዘምሩ መዘምራንን በአንድም ስፍራ አናይም፤ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በሙሉ ብናነብ በቤተክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ በዳዊት ሥርዓት መሠረት መዘምራንን እንድናደራጅ የተነገረን አንድም ቃል የለም:: የእኛ ዳዊታችን ጌታ ኢየሱስ ነው፤ የአዲስ ኪዳኑ ዳዊት ጌታ ኢየሱስ ደግሞ በመዘምራን እየተመሩና እየተገለገሉ ማምለክን ሳይሆን በመንፈስና በእውነት ማምለክን አስተምሮናል:: እርሱ ራሱ የመዘምራን አለ ሲሆን እኛ ሁላችንም ያለመለያየት መዘምራኑ ነን:: በእርሱ እየተመራን ሁላችንም በአንድ ቃል ሆነን በመንፈስ እንዘምራለን:: ቤተክርስቲያን የኢየሱስ ጉባዔ ናት፤ ስለሆነም እርሱ በዚህች ጉባዔ መካከል በመንፈስ ተገኝቶ አብሮን ያመሰግናል፤ «ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፤ በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ» ተብሎ የተነገረው ቃል ስለ እርሱ እንደሆነ በዕብራውያን መልእክት ተነግሮናል/ዕብ2፡13/፤ በስቅለቱ ዋዜማ የእርሱን እራት ለደቀመዛሙርቱ ካበላ በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ጋር አብሮ መዝሙር እንደዘመረ እናነባለን /ማር14፡26/፤ ከዚህ ውጪ ግን በማስተማር ዘመኑ ይከተለው ከነበረው ብዙ ሺህ ሕዝብ መካከል በመጨረሻም አብረውት ከጸኑት ከ120ቹ ሰዎች መካከል መዘምራንን ሲያደራጅ አናይም:: ከእርሱ በኋላም ሐዋርያት በየአገሩ ወንጌልን በመስበክ ሕዝብን በሚሰበሰቡበት ጊዜ መዘምራንን ሲያቆሙ አናይም:: የኋላ ዘመን ሰዎች ግን «ግኖስቲክስ» የሚባሉ ሰዎችና ሌሎች የስህተት አስተማሪዎች ትምህርታቸውን በመዝሙር ያስፋፉ ስለነበር በእነርሱው ዘዴ ትምህርታቸውን ለማፍረስ ሲሉ ደናግል መዘምራንን እያስከተሉ በመዘዋወር ያገለግሉ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፤ ከእነዚህም ሰዎች መካከል ሶሪያዊው ኤፍሬም ይገኝበታል፤ ይህም ቢሆን ወንጌል የሚሰበከው በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወይም በሰው ጥበብ ለዚያውም ሃሰተኞች የተጠቀሙበትን ዘዴ በመከተል ስላልሆነ ተቀባይነት የለውም/1ተሰ1፡5፣ 1ቆሮ2፡5/፤ ሆኖም በዚህ መልኩ ትክክለኛ ባልሆነ መነሻ የተጀመረው የመዘምራን አገልግሎት አሁን የቤተክርስቲያንን ትክክለኛ ባሕርያት ባጡት ጉባኤያት መካከል መደበኛ ሥርዓት ለመሆን በቅቶአል:: ይሁን እንጂ የኋላ ኋላ ሰዎች ይህንኑ የመዘምራን አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ከነበረው የዳዊት መዘምራን አገልግሎት ጋር ለማያያዝ ሙከራ ማድረጋቸው አልቀረም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የዳዊት የመዘምራን አገልግሎት ለአዲስ ኪዳኑ አምልኮ መሠረት ባለመሆኑ ምክንያታቸው ትክክል አይደለም::

> **በአምልኮ ጊዜ እውነተኛ አማኞች ደስታቸው የሚመነጨው እግዚአብሔር እንዲቀርብለት በወደደው መንገድ አምልኮን ለማቅረብ በመቻላቸው ነው**

በዳግመኛ ልደት ከመንፈስ የተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች ዳግመኛ ልደት ባልነበረበት በዳዊት ዘመን የነበረውን ሥርዓት አይከተሉም:: እውነተኛው የአዲስ ኪዳን ዳዊት ጌታ ኢየሱስ እንዳስተማራቸው መንፈስ ከሆነው አዲሱ ልጅነታቸው ጋር እና መንፈስ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣጣመውን የመንፈስና የእውነት አምልኮ በማቅረብ ደስ ይሰኛሉ:: በአምልኮ ጊዜ እውነተኛ አማኞች ደስታቸው የሚመነጨው እግዚአብሔር እንዲቀርብለት በወደደው መንገድ አምልኮን ለማቅረብ በመቻላቸው ነው፤ ከፊታቸው ጌጠኛ ልብስ ለብሰው የተሰለፉ መዘምራንን ባለማየታቸውም ቅር አይሰኙም:: ይልቁንም ከፊታቸው ከሚታዩ ሥጋ ለባሾች እይታ ወጪ ሆነው መንፈስ ለሆነው አምላካቸው በውስጥ ሰውነታቸው በአንድነት በሚያቀርቡት አምልኮ በእጅጉ ይመሰጣሉ::

ከአዲስ ኪዳን አምልኮ ባሕርይ ውጪ የመዘምራንን ቡድን በማደራጀት መገልገሉ በራሱ የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው እንደሚታየው የጠብ፣ የሐሜትና የፉክክር ማዕከልን ማቋቋም መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል፤ በሚለብሱት ልብስ፣ በሚሰለፉበት ቦታ በሚያወጡት ድምፅና ለመታየት በሚያደርጉት እሽቅድምድም በአንድ የመዘምራን ቡድን ውስጥ ያሉት አባላት ብዙውን ጊዜ ፍቅር አይኖራቸውም፤ እንደዚሁም በአንድ ቡድን ያሉት በሌላ ቡድን ካሉት ጋር በመወዳደርና በመቀናናት ቡድናዊነት፣ ወገናዊነትና መለያየት እንዲፈጠር ግንባር ቀደም ሚና ሲጫወቱ ብዙ ጊዜ የሚታዩት የመዘምራን ቡድኖች ናቸው:: ከዚህም አንፃር ያለው ጎጂነት ሊዘነጋና በቀላሉ ሊታይ አይገባም::

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የመዘምራን ቡድን አባል መሆን እንደ አንድ የጸጋ ስጦታ ወይም የአገልግሎት ዘርፍ የሚታይበት ሁኔታም አለ:: በአዲስ ኪዳን ግን በመዘምራንነት በመድረክ ላይ ተሰልፎ ስሕዝብ መዝሙር የማቅረብ አገልግሎት የጸጋ ስጦታ ሆኖ ሲሰጥ አናይም:: የምናገኘው ነገር ቢኖር «ስትሰበሰቡ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፤ ለእያንዳንዱ ትምህርት አለው....» የሚል ነው/1ቆሮ14፡26/፤ ስለሆነም ለአምልኮ በምንሰበሰብበት ጊዜ መዝሙር በልባቸው ያላቸው ሰዎች መዝሙሩን መዘመር ሲጀምሩ አብረናቸው እንዘምራለን፤ አዳዲስ የመዝሙር ቅኔያትን ሊቀኙ የሚችሉ ወገኖችንም ጌታ ለራሱ ያስነሳል፤ እነዚህም ወገኖች መዝሙራቸውን በአካል እየተገኙ ወይም በካሴት እያባዙ ሊያስጠኑን ይችላሉ:: ከዚህ አንፃር መዝሙርን መቀኘት ወይም አዳዲስ መዝሙሮችን ማበርከት ከጸጋ ስጦታዎች ሊመደብ የሚችል አገልግሎት ነው:: መድረክ ላይ ተሰልፎ ስሕዝብ ማቅረብ ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደአገልግሎት ሊወሰድ የሚገባ አይደለም፤ በብሉይ

*(ወደ ገጽ 19 ይዞራል)*

እውነት ቅጽ 1ቁጥር 4

**እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር ዘኅቡእ ዘእምትካት**
**ማቴ13፡35**



**በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውን እናገራ**

## በጸጋው ተጠሩሁ

መንገዱን ሳላውቀው ብዙ ተቅበዘበዝሁ
የርሱን ጽድቅ ትቼ የራሴን ጽድቅ አቆምሁ
ሥርዓትን ሠራሁ ኃጢአትንም ታገልሁ
በሥጋ ሳከብረው አምላኬን ሸነገልሁ
ከበለስ ሥር ሆኜ በረከት ተመኘሁ
የአብርሃም ነኝ ብዬ ራሴን አስመካሁ
በእጄ ያለውን ሳልጥል ሌላ ልይዝ ተጋሁ
ከሞት ፍርሐት ግን የሚያወጣኝ አጣሁ፡፡

ግና
እንደዚህ ስዋትት ብዬ ምን ይዋጠኝ
እኔን የሚቤዠኝ ከፍጡር ሳይገኝ
የመርገም ጨርቅ ሆኖ እኔ ያልኩት ጽድቄ
ይመስለኝ ነበረ የምቀር ወድቄ
እግዚአብሔር ግን አየኝ በፀጋው ተጠራሁ
የእኔም ዘመን ሞልቶ ከወንጌሉ ሰማሁ፡፡

እኔስ
እኔስ ብዬ ነበር እግዚአብሔር ትቶኛል
በዚህ ጠፊ ዓለም ማን ይደርስልኛል?
ለካስ በሸለቆም እግዚአብሔር ያያል
ከተሸሸጉበት መጥቶ ይፈልጋል
ኃጢአተኛን ሰው በፀጋው ይጠራል
ተስፋ የቆረጠን በተስፋ ይሞላል
ቀንበርን ሰባብሮ አርነት ያወጣል፡፡

ታዲያ
ከቶ እንዳልመካ ያለ ምንም ሥራ
በጸጋው አዳነኝ በመስቀል መከራ
ኃጢአቴ በመላ በአንድነት ተሻረ
ለዘላለም መሞት ለዘላለም ቀረ፡፡

አናም
እኔም
ጥሪውን ስቀበል ኢየሱስን ሳምን
አገኘሁ ባምላክ ፊት ተቀባይነትን
ደርሰሃል ተባልኩኝ ከጽዮን ተራራ
ከቅዱሳን አምባ ከሕያዋን ጎራ
ፍሑሐን መላእክት ካደሩበት ስፍራ
ከበኩራት ማህበር ከፍጹማን ተራ፡፡

ከእንግዲህስ
አልሰጋም መልካም እረኛ አለኝ
በቀንና ሌሊት ተግቶ ’ሚጠብቀኝ
ከኋላ ’ሚከተል ከፊት የሚቀድመኝ
መውጣቴን መግባቴን ሁሌ የሚያይልኝ
ባህር ብጣል እንኳ በእጁ የሚያወጣኝ
ለኔስ ጠባቂዬ ኢየሱስ አለልኝ፡፡

አናም
ከእንግዲስ በ ማነው የሚያስፈራኝ?
ምንም ነገር የለም ከጌታ ሚለየኝ
ከእጆቹ መዳፍስ ማነው የሚያወጣኝ?
ኑሮም ባይሳካ ቤቴም ባይሞላልኝ
ዕቅዴም ውጥኔም ከግብ ባይደርስልኝ
ልቤን የሚሞላ የእርሱ ሰላም አለኝ፤
ደግሞስ ምን ይኖራል የምለው ይህ ቀረኝ
ደግሞስ ምን ይኖራል የምለው አነሰኝ
ኢየሱስ በሞቱ ሁሉን ከሠራልኝ
ኢየሱስ በሞቱ ሁሉን ከሆነልኝ፡፡

## «እኔ እኔ አይደለሁም»

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ354-430 የኖረው እውቁ አውግስጢኖስ ጌታን ከማመኑ በፊት እጅግ በከፋ ሁኔታ በአንዲት ሴት የዝሙት ፍቅር ተማርኮ ነበር፤ አማኝ የነበሩት እናቱም ልጃቸው ጌታን እንዲከተልና ሕይወቱ እንዲለወጥ ከልጅነቱ ወራት ጀምረው አብዝተው ይጸልዩለት ነበር፤ እርሱም ልቡ ተከፍሎ በአንድ በኩል ጌታን በሌላ በኩል ያችን ሴት ሲል በሲኦልና በመንግሥተ ሰማያት መካከል የሚዋልል ሰው ሆነ፤ ከዕለታትም በአንዱ በቤታቸው ግቢ በመናፈሻ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ እናቱ በዚያ በመናፈሻው መቀመጫ ላይ የተዉትን የአዲስ ኪዳን መጻሐፍ ቅዱስ ቅጂ አየ፡፡ «ውሰድና አንብብ» የሚል ድምፅም በውስጡ ተሰማው፤ እርሱም መጽሐፍ ቅዱሱን ወስዶ ከፈተ፤ በእርግጥም መንፈስ ቅዱስ ስለመራው ከሮሜ መልእክት ምዕራፍ 13 ያለውን አነበበ፤ በዚያም «ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት አሁን እንደደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቧልና፤ ሌሊቱ አልፎአል፤ ቀኑም ቀርቧል፤ እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃኑን ጋሻ ጦር እንልበስ፤ በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፤ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፤ በክርክርና በቅናት አይሁን፤ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ምኞቱንም እንዲፈጸም ለሥጋ አታስቡ» /ቁ11-14/ የሚለው ንባብ በእጅጉ ልቡን ነካው፤ ውስጡንም ታገለው፤ በመጨረሻም ያነበበውን ለመከተል የሚያስከፍለውን ዋጋ ተመልክቶ ወሰነ፡፡ ከዚህች ቀንም ጀምሮ ሕይወቱ ተለወጠ፤ ከዘህ ልም የተነሣ ኃጢአትን ጠላ፤ ይህንንም ለእናቱ ሲ ነግራቸው እርሳቸውም በእጅጉ ደስ ተሰኙ፡፡ ይሁንና በሚቀጥለው ቀን አውግስጢኖስ በካርቴጅ ጎዳና ላይ ሲጓዝ ሳለ በሕይወቱ ላይ ፈተና የሆነችበትን ቆንጆ ሴት አየ፤ እንደቀድሞው ሊያገኛት አልወደደም፤ እንዳያትም መሮጥ ጀመረ፤ እርሷም በኋላው ልትደርስበት እየሮጠች «አውግስጢኖስ ሆይ ለምን ትሮጣለህ? ጠብቀኝ፤ እኔ ነኝ፣ እኔ ነኝ» እያለች መጮህ ቀጠለች፤ እርሱም እየሮጠ በተራው «እሮጣለሁ፤ ምክንያቱም እኔ--«እኔ»--አይደለሁም» ሲል መልስ እየሰጠ በሽሽቱ ቀጠለ፡፡

## «ስለአንድ በደል ምትክ ሲጠፋ......»

ልጅ ሆኜ የትምህርት ቤት ተማሪ ሳለሁ ልረሳው የማልችለውን አንድ ነገር አየሁ፤ አንድ ሰው ጋሪ ላይ ታስሮ በተወለድኩባት ከተማ አውራ መንገዶች ላይ ይጎተት ነበር፤ በብዙ ሕዝብ ዓይን ፊት እየተጎተተ ጀርባው ከግርፋት የተነሣ እየተቆራረጠ ይደማ ነበር፤ ይህም በጣም አሳፋሪ ቅጣት ነበር፡፡ ይህ ሁሉ የደረሰበት ግን ስለ ብዙ በደሎች ይመስላችኋልን? አልነበረም፤ ስለአንድ በደል ብቻ ነበር፡፡ ከከተማው ነዋሪዎች መካከልም ግርፋቱን ሲጋራው ፈቃደኛ የሆነ አንድ ሰውስ ስንኳ ተገኝቶ ይሆንን? አንድም አልነበረም፡፡ በደሉን የፈጸመው እርሱ ለብቻው ቅጣቱን ተቀበለ፤ የሰውን ሕግ መጣስ የሚያስከትለውን ቅጣት ለብቻው ተቀበለ፡፡

በዩኒቨርሲቲም ተማሪ ሳለሁ ሌላ ልረሳው የማይቻለኝን ነገር አየሁ፤ አንድ ሰው ሲገደል ነው፤ እጆቹ የፊጥኝ ታስረው ነበርና ፊቱም የሞት ያህል የገረጣ ነበር፤ ከወህኒ ቤቱ እየወጣ ሳለም በሺህ የሚቆጠሩ አይኖች ይመለከቱት ነበር፤ ሆኖም ከሚመለከቱት በምትኩ ሲሞት የጠየቀ አንድ ሰው እንኳን አልነበረም፤ ከወዳጆቹ መከከልም ገመዱን በመፍታት «በምትኩ እሞታለሁ ይህን ገመድ በኔ አንገት አግቡት» የሚል አልተገኘም፤ ስለሆነም የሕጉን ውሳኔ ብቻውን ተቀበለ፤ ይህም ሰው እንዲህ የተገደለው ስለብዙ በደሎች ይመስላችኋልን? በፍጹም አልነበረም፤ በሞት የተቀጣው ስለ አንድ ብቻ መተላለፍ ነበር፡፡

ደግሞም ሌላም ሰው አየሁ፤ ጊዜው መቼ እንደሆነ አትጠይቁኝ፤ ያም ሰው በጥፋት ጉድጓድ አፋፍ ላይ ቆሜ የነበርኩና ሲኦል ብቻ የተገባኝ እኔው ራሴ ነበርኩኝ፤ ሲኦል የተገባው የሆንኩት ስለአንድ በደል ነበርን? አልነበረም፤ በማይለዋወጡ የእግዚአብሔር ሕግጋት ላይ ስለተፈጸምኳቸው እጅግ በርካታ ኃጢአቶች ነው፤ ነገር ግን ተመለከትሁ፤ ምትኬ ሆኖ በእኔ ፈንታ የተገረፈ፣ በመስቀል ላይም ስለ እኔ ብዙ፣ ብዙ፣ ብዙ...ኃጢአቶች የሞተ ኢየሱስን አየሁ፡፡ እርሱ ስለ ብዙ ኃጢአቶቼ ሞቷል፤ አየሁም ወደ እርሱም ጮሁኩ፤ ይቅርታንም ተቀበልኩ፤ ስለሆነም እንዲህ ብዬ ዘምራለሁ፤

*«ኢየሱስ በመስቀል ለእኔ ባይሞትልኝ*
*ለዘላለም መሞት ነበር የሚገባኝ*
*ነገር ግን ኢየሱስ ስለ እኔ ሞቶ*
*አዳነኝ በጸጋው ምሕረቱ እጅግ በዝቶ»፡፡*

«ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለቸር ሰው ግን ሲሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል»/ሮሜ5፡7-8/፡፡

(ከሎሮፎርም የተባለውን ንጥረ ነገር ተመራምሮ ያገኘው ጄምስ ሲምሰን ከተናረገው የተወሰደ)

# አዲስ ቅኔ ለበገ

## ከተዋጁት

## «........ቢሆን ኖሮ»

ዓይንህ እንዳየች ቢሆን ፍርድህ
ማን ይቀርባል ወደ ፊትህ?
ኢየሱስ ሆይ..
ሠርክ ዓመፅ ለሆነው ኑሮ
በስህተት ነውር ተዥጐርጕሮ
የህልም ዓለም ተስፋ ቋጥሮ
አርም የልብ ዓይንን አስሮ
ኃጢአት በህሊና ዙፋን ከብሮ
ነገር ሁሉ ተጭበርብሮ
ሰክሮ ተሳክሮ
ነፍዞ ደንዝዞ ተቀብሮ
ታዲያ....................
ዓይንህ እንዳየች ቢሆን ኖሮ
ፍርድህ ቢደርስ ዓመፅ ቆጥሮ
ማን ሊቆም ፊትህ በድፍረት
የሌለበት ዓመፅ ቅጥፈት
ስውር ኃጢአት ንቀት
እረፍት አልባ ዝቅጠት
የእንባ ኑሮ ሸንፈት
ተስፋ መቁረጥ ውድቀት
ሁሌ ጥፋት ሁሌ ኃጢአት
ይህን መልቀቅ ያንን ማምጣት
ዓመፅ ወዶ ጽድቅን መጥላት
ሞትን አቅፎ ሕይወት መግፋት
ክብርን ረግጦ ውርደት ማንሳት
ማን ሊቆም ፊትህ በብቃ
............ ሲያንሰን ቅጣት
............ ሲያንሰን ጥቃ
የኛ ግሣት ..................
ሠርክ ኃጢአት ............
ሁሌ ክፋት .................
ይህን አይተህ ቢሆን ፍርድህ
ይህን ሰምተህ ቢሆን ጽድቅህ
ማን ይቆማል ደፍሮ ፊትህ
ልፍረድ ብትል የኛ ጌታ
ፅህ ብ’ጥል ፅህ ሠርታ
ብትጨሳልም ፀሐይ ጠፍታ
ማን ተው ሲልህ
ማን ሲያስቆምህ
ማን ሲያግድህ
ያስፍቅርህ
ቢበዛልን ቸርነትህ
ምህረትህ
ደግነትህ
ቿንቿ አልባው ጥልቅ ፍቅርህ
...................ጥልቅ ምክርህ
...........ባይሆን ኖሮ በጐነትህ
እኛም ጠፍተን እንደጠፉት
እኛም ሞተን እንደሞቱት
ተስፋ አጥተን ተስፋ እንዳጡት
ቀርተን ነበር እንደቀሩት
በአውሬው ክፋት እንደከፉት
በአባብ ምክር እንደሳቱት
አልቀን ነበር እንዳለቁት፡፡
ግና ኢየሱስ...................
አይሁን ብትል ሳይሆን ቀረ
ፍቅርህ በልጣ ሞት ተሻረ
እኛ ኖረን እርሱ አፈረ፡፡
አይ ምህረትህ
አያልቅብህ
አይጎድልብህ
አይፀፅትህ፡፡
መች እንዳይንህ
በማየትህ
እንደ ጆሮህ
በመስማትህ
አልጠፋንም በልጦ ፍቅርህ
ስለጭንቅህ
በመስቀልህ
በሥቃይህ
መታረድህ
ስለሞትህ
መቤዠትህ
መሥዋዕትህ
ንጹህ ፍቅርህ
ቅዱስ ፅህ
ነጻ ጽድቅህ
ውድ ደምህ
ክቡር ስምህ
አኑሮናል ምህረትህ
ደግፎናል ቸርነትህ
አቁሞናል ደግነትህ፡፡
......እንጂ ኢየሱስ
መች እንዳ’ይንህ
ጉዳችንን በማየትህ
ሞት ነበረ ጻድቅ ፍርድህ፤
አይገርምም ወይ
ሞታችንን በመሞትህ
ቁስላችንን በመቁሰልህ
ፍርዳችንን መገልበጥህ
ህልማችንን መስወጥህ
ዐይንህ አይቶ መታገሥህ
ጆሮህ ሰምቶ መራራትህ
አይገርምም ወይ
የማያልቀው ምህረትህ
ወሰን አልባው ቸርነትህ፡፡
ታዲያ ኢየሱስ..
ምን ይምጣልህ
ይቅረብልህ
ሕዝብህ ላንተ ምን ያርግልህ?
ወርቅ ገንዘብ ወይስ ዕንቁ?
ዕጣን ከርቤ ወይስ ሽቱ?
እናጨብጭብ?
እናሸብሽብ?
እልል እንበል?
ወይስ ሆታ? ወይ እሪታ? ምን እናክል?
ከበሮውን እየደለቅን እን-ጨፍር?
ምን እናምጣ ምን እንደርድር
በገናውን ወይ ቤዝጊታር?
ያንሳል ብለን ምን እንፍጠር?
እንደእንቦሳ እንፈንጭልህ? እመር እመር!
ሀገር ምድር በሑሑታ እናሸብር?
እውን ላንተ ምን እንገብር?
ምን እንጨምር?
ምን እንቀንስ ምን እንደምር?
ግና ኢየሱስ......
ይሄ ሁሉ አይመጥንም አንተነትህን
አይስማማም ባሕርይህን
አያስደስት መሻትህን
አያረካ አባትህን፡፡
ስለዚህም በዚህ ፈንታ...
በመገረም
በመደነቅ በመደመም
ልባችንን ላንተ ሰጥተን
እውነት መንፈስ እየመራን
እናምልክህ ፊትህ ወድቀን
ከዚህ በቀር ሌላም የለን፤
ይኸው ቅኔው ላንተ ክብር
የምትሻው ፍሬ ከንፈር ፤
***«ቢሆን ኖሮ የኛ ኑሮ***
***ባላኖርከን ድሮ ድሮ***
***ግን አልሆነም ሞት ተሽሮ***
***ይኸው አለን ጸጋ ከብሮ»፡፡***
■



## እንነሣና....... ከገጽ 12 የዞረ

*መንፈሳዊ ሠራተኞች ሥራውን ከሕዝቡ ጋር አብረው ሊሠሩ ይፈቅዳሉ፤ እግዚአ ብሔር በልባቸው ያኖረውን ሥራ ለማካፈልና አብሮም ለመሥራት ምንም አይሰስቱም፡፡*

የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች፤

*ለእኛ ቅጥራችን እውነተኛውን አማኝ ከአፍ አማኙና ከከሃዲው ዓለም የሚለይ ከጌታና ከሐዋርያት የተቀበልነው ትምህርትና ክርስቲያናዊ የሆነው ምግባር ነው፤ ለእኛ በምድር የምትኖር ኢየሩሳሌም የለችንም፤ በተግባር የክርስቶስ ጠላት ሆኖ ወደመኖር የገቡትን መለካውያን የክርስትና ሥርዓተ ሃይማኖቶችን ለማደስ የሚደረግ እንቅስቄም እንደራእይ ተቆጥሮ ይኸው ስለነህምያ የተጻፈው ታሪክ እየተጠቀሰለት ቢገኟም የሉን መንፈስ ለሚከተሉ ደቀመዛሙርት ግን እነዚህ ከሉ የራቁ የሃይማኖት ድርጅቶች ቅጥሯ የፈረሰባት ኢየሩሳሌም አይደሉም፤ በምትኩ ግን እነዚህን ደቀመዛሙርት ከአፍ አማኙና ከከሃዲው ዓለም የሚለዩ ከመለኮታዊ ምንጭ የፈለቁና የተቀደሱ የክርስትና ሥነምግባሮች፣ እሴቶች፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች፣ በጥቅሉ ከጌታና ከሐዋርያቱ የተገኙ ትምህርቶች የነበሯቸውና አሁን ግን እነዚህ መንፈሳዊ ነገሮች የሌሏቸው አማኞች ቅጥሯ የፈረሰባት ኢየሩሳሌም ናቸው፤ በመንገድ ዳር የወደቀውን መልቀምና በአዝመራው መካከል እንክርዳድን መዝራት ልማዱ የሆነ ጠላትም ብዙ አማኞችን ከኢአማንያን የሚለዩአቸውን ቅጥሮች እንዳፈረሰባቸው ማየት ይቻላል፡፡*

*ታዲያ በዘመናችን በአማኞች ዙሪያ ብዙ የፈረሰ ቅጥር እንዳለ ስናስብ ምን ይሰማናል? በየዘመናቱ ካለው የሰው ልጅ ሥልጣኔ ጋር ራሱን እያስማማ መልኩንም እየቀያየረ ብቅ የሚለው ሰይጣን አማኞችንም ሊቀበሉት በሚችሉት መመሳሰል እየቀረበ ማለትም እንደ ጳውሎስ አገላለጽ «የብርሃን መልአክ» መስሎ እየተገለጠ ቅጠራቸውን በማፈራረስ ላይ እንደሆነ ይታወፅ፡፡ ሰይጣን እንደናቡከደነፆር በግልጥ መጥቶ የአማኞችን ቅጥር ሊያፈርስ ቢሞክር ማንነቱ ስለሚታወቅበት ብዙም ላይሳካለት ይችላል፤ ስለዚህ በመመሳሳል እየቀረበ ሊነቁበት ያልቻሉ የምስኪን አማኞችን ቅጥር ሊያፈራርስ ይጥራል፤ ቅጥር አንድን ከተማ ከክፉ የሚከልል ለነዋሪዎቿም በጥቂቱም ቢሆን ዋስትና ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ ነገር ነው፡፡ ቅጥር በዙሪያው የተለያዩ በሮች ስለሚኖሩት ወደ ከተማይቱ የሚገቡትንና የሚወጡትን ሁሉ ለመቆጣጠር አመቺ ይሆናል፤ ለጥበና ለጥንቋ የቅጥር መኖር አስፈላጊ ነው፤ ቅጥር ሲፈርስ ግን ከተማይቱ ለዘራፊዎች ሆነ ለሌሎች የሚያጠቁ ኃይላት የተጋለጠች ትሆናለች፡፡ አማኞች ደግሞ ከአጋንንትና አጋንንት ከሚልኳቸው አሳቾች ከዚህችም ዓለም ተንኰለኛ ሠራተኞች እንዲሁም የክፉት መልእክተኞች ሊጠበቁ የሚችሉት መንፈሳዊ ቅጥር ሲኖራቸው ነው፤ አማኞች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና የእርሱ ሐዋርያት ያስተማሩንን የወንጌል እውነት ጠንቅቀው ቢረዱና ወደ መረዳት ባለጠግነትም ቢደርሱ በዚያም በተረዱትም እውነት ቢኖሩና ተግባራዊ ክርስትና ቢታይባቸው ቅጥራቸው የጸና ይሆናል፤ ሆኖም ብዙዎች እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት በውሸተኞች ሐዋርያት አማካቿነት በተሰበከ ልዩ ወንጌል ምክንያት ሊኖሩበት የሚገባቸው የእውነተኛው ወንጌል ቅጥር ፈርሶባቸው ይታያል፤ ይህም ማለት አንድ ሰው ክርስቲያን ነኝ እያለ የጌታንና የሐዋርያትን ትምህርት የሚፃም አካሄድ ባለው በጠላት አሠራር ሙሉ በሙሉ ተጠቂ ሆኗል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም በተሳሳተ መሠረት ላይ በሚገነባ እምነትና ትምህርት ምክንያት በአማኞች መካከል ይህ ነው የማይባል የሥነ-ምግባር ውድቀት ሲታይ ቅጥሩ ምን ያህል እንደፈረሰ ለማየት ይቻላል፡፡ አንዳንዱ የሥነ-ምግባር ውድቀት በካዱት እንኳ የማይታይ እስኪሆንና ከሃድያንም ለመሳለቅ እስኪያመቻቸው ድረስ ብዙ የፈራረሰ ነገር እንዳለ እናያለን፡፡ ታዲያ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እውነትን ካለመቀበል*

*(ወደ ገጽ 20 ይዞራል)*

# የአንባብያን

**«ተሰናአዉ ኵልክሙ እለ በክርስቶስ ሀሉክሙ»**
/1ጴጥ5፡14/፡፡



# ዓምድ

**«በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሠላም ይሁን»**
/1ጴጥ5፡14/

በዚህ ዓምድ ሥር ከአንባቢያን የሚደርሱን አስተያየቶችና ጥያቄዎች ይስተናገዳሉ፤

⇒ ለእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች፣

ለጤንነታችሁ እንደምን አላችሁ እያልኩኝ ከዚህ በመቀጠል ሐሳቤን እገልጣለሁ፤ ጽሑፋችሁን ሰው ጋብዞኝ ካየሁት በኋላ በይበልጥ ከእናንተ ለመረዳት በጻፍኩት ደብዳቤ መሠረት እውነት ጋዜጣንና ጦማረ ጽድቅ የሚል መጽሐፍ ልካችሁልኛል፤ በዚህም ከልቤ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁኝ፤ እናንተንም እግዚአብሔር ይባርካችሁ እላለሁ፤ በእውነቱ ጽሑፋችሁ ዓይኔን ከፍቶልኛል፤ ሰውነቴም በጣም ደስ ብሏታል፡፡

በተረፈ አንድ ግራ ያጋባኝ ነገር አለ፤ መቼም «የማንንም ሃይማኖት ደግፈን ወይም ወክለን አልቆምንም የእግዚአብሔርን እውነት እንጂ» ብላችኋል፤ ይህ አባባላችሁ ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡ ታዲያ የእግዚአብሔርን እውነት ማለትም ለእኛ የሞተውንና የተነሳውን አምላክ ክርስቶስን በጽሑፋችሁ ስትገልጡት በ66ቱ የፕሮቴስታንት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ ለምን በጽሑፋችሁ ውስጥ ከብሉይ ኪዳን 2ኛ የቀኖና መጻሕፍት ውስጥ ጥቅስ አልተጠቀማችሁም? ስለዚህ ነገር ለማወቅ ስለምፈልግ ብታስረዱኝ እወዳለሁ፡፡

አቶ ግርማ ፍስሐ
አዲስ አበባ

**ከአዘጋጆች፡-** ከእውነት ጋዜጣና ከጦማረ ጽድቅ ላይ ያነበቡት የእውነት ቃል ለነፍስዎ ደስታን በመስጠቱ እግዚአብሔርን አመስግነናል፡፡ ግራ ያጋባዎትን ጥያቄ ማንሳትዎም አግባብነት ያለው ከመሆኑም ባሻገር የብዙዎችም ጥያቄ በመሆኑ እንደሚከተለው መልስ ተሰጥቶበታል፡፡

አማኞች ለእምነታቸው ማስረጃ አድርገው የሚጠቅሱት መጽሐፍ «መጽሐፍ ቅዱስ» ብቻ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ተብሎ ለሁለት ይከፈላል፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በ1ኛ ደረጃ ቀኖናውያን ተደርገው ተቀባይነት ያገኙት ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ሚልክያስ የሚገኙት መጻሕፍት 39 ናቸው፡፡

ከነዚህ መጻሕፍት ሌላ «ተጨማሪ» ተደርገው የተወሰዱትና ዲዮትሮ ካኖኒካልስ/2ኛ ቀኖናውያን/ የሚባሉት መጻሕፍት ግን ከጥንት ጀምሮ በአይሁድም ሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ ይፋ የሆነ ተቀባይነት አላገኙም፡፡ «ቩልጌት» የተባለውን የላቲን ትርጉም የሠራው «ጀሮም» የተባለው ሮማዊ እነዚህን መጻሕፍት «አፖክሪፋ» ብሎ ጠርቷቸዋል፤ ትርጉሙም ኅቡዓት /የተደበቁ/ ማለት ነው፤ እስከ አሁንም አፖክሪፋ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ እነዚህ ብዙዎች የማይተማመኑባቸው ኅቡዓት ወይም ስውር የሆኑ መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መሆን አልቻሉም፡፡ «2ኛ የቀኖና መጻሕፍት» የሚለው አባባልም በኋላ ዘመን የተጀመረ ሲሆን በደረጃቸው ከዘፍጥረት እስከ ሚልክያስ ከሚገኙት መጻሕፍት ዝቅ ያሉ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የሚቀበሏቸውም ሰዎች እንኳ ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል ለመቀበል እንዳልቻሉ ከተሰጠው ስያሜ መረዳት ይቻላል፤ 66ቱን ቅዱሳት መጻሕፍት ግን የፕሮቴስታንት መጻሕፍት ናቸው ብሎ ከፕሮቴስታንቶች ጋር መፈረጁ በእውነተኛ አማኞች ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከሃይማኖት ድርጅት አንፃርም ብንመለከት 66ቱን ቅዱሳት መጻሕፍት ካቶሊካውያንና ኦርቶዶክሳውያንም ይቀበሏቸዋል፡፡ ልዩነቱ ያለው በ66ቱ ላይ ሳይሆን በተጨማሪዎቹ መጻሕፍት ላይ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ላይ የተጨመሩት የአፖክሪፋ መጻሕፍትም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ዕዝራ ቀዳማዊ
2. ዕዝራ ካልዕ
3. መጽሐፈ ጦቢት
4. መጽሐፈ ዮዲት
5. መጽሐፈ አስቴር/በዋናው መጽሐፈ አስቴር የማይገኙ ምዕራፋት/
6. መጽሐፈ ጥበበ ሰሎሞን
7. መጽሐፈ ሲራክ
8. መጽሐፈ ባሮክ (መልእክተ ኤርምያስን ጨምሮ)
9. መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ
10. ሶስና
11. ተረፈ ዳንኤል
12. ጸሎተ ምናሴ
13. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
14. መጽሐፈ መቃብያን ካልእ

እነዚህ መጻሕፍት ብዙዎቹ ብሉይ ኪዳን በተጻፈበት በዕብራይስጥ ቋንቋ የተጻፉ አልነበሩም፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጨመሩትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ285 ሰባው ሊናት ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ በተረጎሙ ጊዜ ነው፡፡ ሆኖም አይሁድ በ90 ዓ.ም ጃምኒያ በተባለች ቦታ ባደረጉት ጉባዔ እነዚህ መጻሕፍት በቀኖናው ተቀባይነት እንደሌላቸው ገልጸዋል፤ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዘንድም ከዘፍጥረት እስከ ሚልክያስ እንዳሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ተቀባይነት አላገኙም፤ በዘመነ ሐዋርያት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሲጻፉ ከእነዚህ የአፖክሪፋ መጻሕፍት ውስጥ አንድም ጥቅስ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ተጠቅሶ አለመገኘቱ በዚያን ጊዜ በኖሩ አማኞች ዘንድም ተቀባይነት አለማግኘታቸውን ያሳያል፡፡ ከዚያ በኋላም እነዚህ መጻሕፍት በቤተክርስቲያን ደረጃ ተቀባይነት ሳያገኙ ቆይተዋል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ እነዚህን መጻሕፍት በ2ኛ ቀኖናዊነት የተቀበሉት የሮማ ካቶሊካውያን ናቸው፤ ይህንንም የወሰኑት በ1546 ዓ.ም. ባደረጉት የትሬንት ጉባዔ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አማኞች ያልተቀበሏቸውን እነዚህን መጻሕፍት የተቀበለው ይህ የትሬንቱ ጉባዔ ብዙ መንፈሳዊ ውድቀት በነበረበት ሁኔታ በዚያ ዘመን የወሰነው ውሳኔ በእውነተኛ አማኞች ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት የብሉይ ኪዳን 2ኛ ቀኖናውያን መጻሕፍት ተጨማሪ ተብለው ከመጠራታቸውም ሌላ ከላይ ከተጠቀሱት አሥራ አራት መጻሕፍት ውጪ ተረፈ ኤርምያስ፤ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሄኖክ የተባሉ መጻሕፍትንም ጨምረው ይዘዋል፡፡ መጻሕፍተ መቃብያን ደግሞ ሦስት ሲሆኑ በይዘታቸውም ከላይ በዝርዝሩ ውስጥ ከተጠቀሱት ሁለቱ መጻሕፍተ መቃብያን ፈጽሞ የተለዩ ናቸው፡፡

ጠቅለል ለማድረግ እነዚህ የአፖክሪፋ መጻሕፍት በሚከተሉት ምክንያቶች ተቀባይት የላቸውም፡፡

1ኛ/ ሐዋርያትም ሆኑ ከእነርሱ በኋላ የነበሩ እውነተኛ የወንጌል አገልጋዮች እነዚህን አይሁድ ያልተቀበሏቸውን መጻሕፍት አልተቀበሏቸውም፤ ከዚያ ይልቅ ግን አይሁድ የተቀበሏቸውን መጻሕፍት ብቻ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አድርጎ መቀበል እንደሚገባ ተናግረዋል፤ ለምሳሌ ከ170-190 ዓ.ም. ያገለግል እንደነበር የሚታወቀው የሰርዴሱ ሜሊቶስ ከዕብራይስጡ የአይሁድ ቀኖና ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል ዝርዝር ትቶ አልፏል፤ እንደዚህም በቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና ታሪክ ውስጥ ታዋቂ የሆነው ከ295-373 የኖረው የእስክንድርያው አትናቴዎስም ብሉይ ኪዳንን አስመልክቶ ሲጽፍ ክርስቲያኖች ዕብራውያን ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው ያሏቸው መጻሕፍት ብቻ ሊኖሯቸው ይገባል ብሏል፡፡

2ኛ/ በሮሜ መልእክት ውስጥ የብሉይ ኪዳን ቃት ለእስራኤል እንደተሰጡ የሚያስረዱ ንባቦች አሉ፡፡ በሮሜ3፡2 «አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃት አደራ ተሰጡአቸው» የሚል ስናነብ በሮሜ9፡4

*(ወደ ገጽ 17 የዞረ)*

## የአንባብያን .. ..ከገጽ 16 የዞረ

ላይ ደግሞ «እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መስጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃት ለእነርሱ ናቸውና» የሚል ል እናነባለን፤ ስለሆነም እነ አትናቴዎስ እንዳሉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በተመለከተ አይሁድ የወሰኑትን ቀኖና መቀበሉ ተገቢ ነው፤ አማኞች እነርሱ የተቀበሏቸውን መጻሕፍት ብቻ ሊቀበሉ ይገባቸዋል።

3ኛ/ በእነዚህ የአፖክሪፋ መጻሕፍት ውስጥ ስህተት ይገኛባቸዋል ለምሳሌ: በመጽሐፈ ጦቢት12:9 ላይ ምጽዋት ከሞት ታድናለችና ከኃጢአትም ሁሉ ታነፃለችና ወርቅ ከማድለብ ምጽዋት መስጠት ይሻላል ይላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰው ከኃጢአቱ የሚነጻው «የኃጢአት መሥዋዕት» ቀርቦለት ነው፤ «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» በተባለው መሠረት የደም መሥዋዕት ሳይቀርብ ከኃጢአት መንጻት አይቻልም/ዕብ9:22/፤ መጽሐፈ ጦቢት ግን ይህን በመረን ምጽዋት ከኃጢአት ሁሉ ታነጻለች በማለቱ ተሳስቷል። እንደዚሁም በአማርኛው የአፖክሪፋ መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ «ተረፈ ኤርምያስ» የተባለው መጽሐፍ ከእነዚህ መጻሕፍት ጋር የተጠቀሰ ሲሆን በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ኤርምያስ ወደባቢሎን ከሕዝቡ ጋር አብሮ እንደተማረከ ይገልጣል /ተረፈ.ኤር.9:15-16፤10:25/፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ኤርምያስ ከጎዶልያስ ጋር ሳይማረክ እንደቀረና በኋላም ወደግብፅ እንደሄደ ይናገራል/ኤር43:6-7/፤ ይህም ተረፈ ኤርምያስ ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር እንደሚረን ያስረዳል። በዚህ ዓይነት ለጊዜው ያልዘረዘርናቸው የታሪክ፣ የመልክዓምድሮችና የዶክትሪን ስህተቶችን ይዘው ስለሚገኙ በመጽሐፍ ቅዱስነት ልንቀበላቸው አልቻልንም። ስለሆነም እነዚህን መጻሕፍት በእውነት ጋዜጣም ሆነ በመጻሕፍቶቻችን ሁሉ **በመጽሐፍ ቅዱስነት** አንጠቀሳቸውም። የያዙትን ስህተት ለመግለጥ ወይም ከሚናገሩት ቃት መካከል ከያዝነው ርእስ ጋር በተያያዘ መልኩ የተባለ ነገር ካለ ለማነጻጸር ያህል አልፎ አልፎ ልንጠቅሳቸው እንችል ይሆናል እንጂ እንደ እግዚአብሔር ል አንቀበላቸውም። የምንቀበላቸውም ከእውነት ጋር በመወገን ነው እንጂ ጠያቂያችን እንደገመቱት ከፕሮቴስታንቶች ጋር በመወገን አይደለም።

ለጠያቂያችን መልስ ለመስጠት ያህል ይህን ካልን ዘንድ ወደፊት በእነዚህና በሌሎቹም የአፖክሪፋ ጽሑፋት ላይ የተጠኑ ጽሑፎችን በስፋት እንደምናቀርብ በዚህ አጋጣሚ ልንገልጥ እንወዳለን።

⇒ ለእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች፣

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ እላለሁ። የላካችሁልኝ «እውነት» ጋዜጣና «መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው መለኮት ነው» የሚለው መጽሐፍ ደርሰውኛል፤ አንብቤ ትምህርት አግኝቼበታለሁ።

አንድ ጥያቄ አለኝ፤ በ1ኛ ዮሐንስ መልእክት ላይ «ሞት የማይገባው ኃጢአት አለ» ይላል ምን ማለት ነው? ብታብራሩልኝ።

ሙንድኖ ኪዱ
አሳባ ቁሊቶ

**ከአዘጋጆች፣** «ሞት የማይገባው ኃጢአት አለ» የሚለው ንባብ የሚገኘው በ1ዮሐ5:16 ላይ ነው፤ ሙሉ ሉም የሚከተለው ነው «ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፤ ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ሳደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል። ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፤ ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም» ይላል /1ዮሐ5:16/፤ በዚህ ንባብ ውስጥ ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሳደረገ ወንድም አማኝ ሊጸልይ /ሊለምን/ እንደሚገባው ተገልጧል። ልመና የሚቀርብለት ሰው «ወንድም» ተብሎ ስለተጠራ በኢየሱስ አምኖ የዳነ ሰው እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ስለዚህ ሞት «የማይገባው ኃጢአት» የሚለው አማኝ ከሥጋ የተነሳ የሚሠራውን ኃጢአት ነው። አማኝ በሚሠራው ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ሊቀጣው ይችላል/ዕብ12:6-11/፤ ቅጣቱም በሞት ሊሆን ይችላል፤ አንዳንድ ወንድሞች የሚፈጽሙት ኃጢአት ለሞት የሚያበቃ ሊሆን ይችላልና፤ ለምሳሌ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የአባቱን ሚስት ያገባውን ሰው በተመለከተ «ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው» የሚል ል ተጽፎአል /1ቆሮ5:1-5/፤ እንዲሁም ሐናንያና ሰጲራ ለሞት የሚያበቃ ኃጢአትን ፈጽመው ስለነበረ በእግዚአብሔር ፍርድ ሞቱ /ሐዋ.ሥራ5:1-11/፤ ከቆሮንቶስ አማኞች መካከል አንዳንዶቹ ለጌታ እራት የማይገቡ ስለ ነበሩ ሞቱ /1ቆሮ11:27-30/፤ ስለእነዚህ ሰዎች ልንለምን አልታዘዝንም፤ ሆኖም በሞት ለመቀጣት የሚያበቃ ነገር ግን እንደ በሽታ ያለ ቅጣትን የሚያመጣ ኃጢአትን ለፈጸመ ወንድም ልንለምን ይገባናል። በያዕ5:15 ላይ «የእምነት ጸሎት ድውዩን ያድናል፤ ጌታም ያስነሳዋል ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል። እርስ በእርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፤ ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለች» ይላል። ስለዚህ ከሞት ያነሰ ቅጣት የሚገባውን ኃጢአት ሳደረገ ሰው ብንጸልይለት ያ ወንድም ሕይወትን ያገኛል። ይህም ማለት የዘላለም ህይወትን ሳይሆን በኃጢአቱ ምክንያት ተበላሽቶ የነበረው ከእግዚአብሔርና ከአማኞች ጋር ያለው ኅብረት ይታደስለታል ማለት ነው። ምክንያቱም ሰው የዘላለምን ሕይወት የሚያገኘው ኢየሱስን ባመነ ጊዜ እንደሆነ በዚያው ጥያቄው መሠረት ባደረገው መልእክትና ምዕራፍ ተገልጧልና/1ዮሐ5:13 ተመልከት/።

⇒ በክርስቶስ ፍቅር የታተማችሁ ውድ የእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች፤

የእግዚአብሔር ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። በአድራሻዬ የላካችሁልኝ መጻሕፍትም ሆኑ ሁለት የእውነት ጋዜጦች ደርሰውኛል፤ በጣም አመሰግናችኋለሁ፤ ጌታ ይባርካችሁ። በውስጣቸውም ብዙ ትምህርት ያዘሉና በዚህ ዘመን ላለን ወጣቶች ሕይወትን የሚለውጥ በጌታም ፍቅር እንድንኖር የሚያደርግ ልን የያዙ በመሆናቸው በጣም ተደስቻለሁ፤ ለወደፊቱም የበለጠ ውን እንደምታዘጋጁ እርግጠኛ ነኝ፤ ጌታ ኃይልና ብርታቱን ይስጣችሁ፤ እኔም አንዳንድ ያልተረዳኋቸው ጥያቄዎች አሉኝና ላቅርብላችሁ: - በሮሜ8:34 ላይ «ማጽደቅና መኰነን የሚችል» ሲል ፍርድን ያመለክታል፤ ታዲያ እንዲህ ከሆነ አማላጅ ማነው? ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ነው እንላለን? ለእኔ ያልገባኝ ነገር ቢኖር «እኔና አብ አንድ ነን»/ዮሐ10:30/ በሚለው መሠረት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ /ሥላሴ/ አንድ አምላክ ከሆኑ፣ መተናነስና መበላለጥም ከሌላቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ወዴት ያማልዳል? በዮሐ16:26 ላይስ «...በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለእናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም» የሚለውስ ምን ማለቱ ነው።

ሚሚ ስማ
ከወሳይታ ሶዶ

**ከአዘጋጁ፣** በቅድሚያ በሮሜ8:33-34 ላይ ያለውን ል እንመልከት፤ «እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኰንንስ ማነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» ይላል። ሐዋርያው ጳውሎስ የሮሜን መልእክት የጻፈው ጌታችን ዐርጎ በእግዚአብሔር ቀኝ ከተቀመጠ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። በዚህም መልእክቱ ውስጥ በጥቅሱ እንደተመለከትነው «በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለእኛ የሚማልደው ክርስቶስ ነው» ብሏል። ሐዋርያው በሮሜ1:16 ላይ በወንጌል አላፍርም ባለው መሠረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን «ስለ እኛ የሚማልደው» ብሎ ሲገልጠው ምንም አላፈረም። በእርግጥ ይህ ስለ እኛ የሚማልደው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያጸድቀውና የሚኰንነው እግዚአብሔር መሆኑ ግልጥ ነው፤ በቁ.33 ላይ የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ የሚኰንንስ ማነው? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ «የሞተው ይልቁንም

(ወደ ገጽ 18 የዞረ)

## የአንባብያን .. ከገጽ 17 የዞረ

ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኛ ያለው ደግሞ ስለ <u>እኛ የሚማልደው</u> ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» የሚል መልስ የተሰጠውም ለዚሁ ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚፈርድ አምላክ መሆኑ በብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል የተመሰከረ ስለሆነ በምንም መልኩ የሚያጠያይቅ አይደለም፤ ሆኖም መታወቅ ያለበት ኢየሱስ ለእኛ የሚማልድ ሰው መሆኑም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የዚያኑ ያህል በስፋት መነገሩ ነው:: ኢየሱሰ ፍጹም አምላክ ብቻ ሳይሆን ፈጹም ሰውም ነው:: «እኔና አብ አንድ ነን» ብሎ የተናገረውም በመለኮቱ ከአባቱ ጋር ያለውን አንድነት ለመግለጥ ነው፤ በሰውነቱ ግን ሞትን ሞቶ ነበርና በዚህ ከመላእክት እንኳ በጥቂቱ አንሶ እንደነበር ተነግሮለታል /ዕብ2:9/፤ በሰውነቱ የሃይማ ኖታችን ሐዋርያና ሊቀካህናት ነው /ዕብ3:1/፤ በእግዚአብሔር ቀኛ የተቀመጠውም በሰውነቱ ነው:: ምክን ያቱም ሉ <u>የሞተው</u>፣ ይልቁንም <u>ከሙታን የተነሳው</u> ካለ በኋላ <u>በእግዚአብሔር ቀኛ ያለው</u> በማለት ይናገራልና:: «በእግዚአብሔር ቀኛ ያለው» ከሚለው በፊት የተነገሩት «የሞተው፤ ከሙታን የተነሣው» የሚሉት ቃት ሰውነትን በግልጽ ስለሚያመለክቱ ኢየሱስ በእግዚአብሐር ቀኛ የተቀመጠው ከሰውነቱ ሳይለይ መሆኑን እንረዳለን:: እንዲሁም በሐዋ.ሥራ1:9 ላይም ጌታ ኢየሱስ እያዩት እንዳረገና ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ እንደተቀበለችው እናነባለን፤ ካረገ በኋላም እስጢፋኖስ ሰማይ ተከፍቶ በእግዚአብሐር ቀኛ ያየው «የሰው ልጅ» እንደሆነ ተጽፎአል /ሐዋ.ሥራ7:56/:: ዳግመኛም ጌታ ኢየሱስ ለሳውል ሲገለጥ «አንተ የምታሳድደኛ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኛ» ብሎታል/ሐዋ.ሥራ21:8-9/፤ ካረገ ከብዙ ዓመታት በኋላም ለዮሐንስ በራእይ ሲገለጥለት «ሞቼ ነበርሁ፤ እነሆም ከዘላለም እስከዘላለም ሕያው ነኛ» ብሎታል/ራእ1:18/፤ እነዚህ ሁሉ ጥቅሶች ጌታ ኢየሱስ ካረገም በኋላ በአምላክነት ብቻ ሳይሆን በትስብእቱም/በሰውነቱም/ እንዳለ የሚያስረዱ ናቸው:: ስለዚህ በምድር እያለ ሲማልድ በሰውነቱ እንደሆነ ሁሉ በእግዚአብሔር ቀኛም የሚማልደው በሰውነቱ ነው:: በምድር ላይ በሰውነቱ ሲማልድ ከአባቱ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን አንድነት የማያጠፋ እንደሆነ ሁሉ በእግዚአ ብሔር ቀኛም ሆኖ ሲማልድ መለኮታዊ አንድነቱ እንደተጠበቀ ነው:: መለኮቱና ሰውነቱ የተዋሐዱት በተዐቅቦ /በመጠባበቅ/ መሆኑ በጠያቂያችን ሊዘነጋ አይገባም::

በዮሐ16:26 ላይ «በዚያን ጊዜ ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም» የሚለው ካረገ በኋላ እንደማያማልድ የሚያመለክት አይደለም፤ እርሱ በምድር ላይ አብሮአቸው በአካል እያለ ስለ እነርሱ ይለምንላቸው ነበር፤ ሲለያቸው ግን በምድር ላይ እንደ በፊቱ የሚለምንላቸው አይደለም:: በዚህ ምትክ ግን «በስሙ ይለምናሉ»፤ በዚህም መሠረት ዛሬም ቢሆን ኢየሱስ የሚማልደው በሰማይ በእግዚአብሔር ቀኛ ሆኖ ነው እንጂ በምድር ሆኖ አይደለም፤ በምድር ግን እኛ በስሙ እንጸልያለን:: እርሱ በሰማይ የሚያደረገው ምልጃም በባሕርዩ ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ እንዳልሆነም ሊስተዋል ይገባል::

ከዚህ በተረፈ ጠያቂያችንም ሆኑ ሌሎች ይህ ጥያቄ ያላችሁ ወገኖች «የአዲስ ኪዳን መካከለኛ» በሚል ርእስ በዚሁ አገልግሎት የታተመውን መጽሐፍ በመመልከት ሰፊ ማብራሪያ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን ሳንጠቁም አናልፍም::

## አስተያየቶች፣

⇒ ለእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች፣

በክርስቶስ ኢየሱስ በመድኃኒታችን ስም ሰላም እላችኋለሁ፤ በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ::

እውነት ጋዜጣ ቅጽ.1 ቁ.2 ውስጥ «በአገልግሎት ዓምድ» ሥር ባለው «አገልግሎት መሥዋዕት ነው» በሚለው ጽሑፍ ላይ ጥቂት ልበል:: እውነትን በመግለጥ የሚገባችሁን ብላችኋል፤ ጌታ ይባርካችሁ:: እናንተ ያላችሁት ደግሞ በትክክል እውነት ነው፤ የዘመኑም ችግር ነው:: ዛሬ ዛሬ አገልግሎት ከመብት ቀጥሎ እየታየ ነው:: መብቴ ካልተጠበቀ ለምን? ..... እየተባለ፤ ግን እውነቱ ሲታይ እንዲህ አይደለም፤ ጌታ ክርስቶስ መርገማችንን ሊሸከም ሲመጣ ለዚህ ጉዳይ ያስቀመጠው የመብት ቅድመ ሁኔታ ፈጽሞ አልነበረም፤ መሥዋዕት ከፍሎ እኛን ዋጀ፤ መከሩ ገና ብዙ ነው፤ የጌታም መምጣት እየቀረበ ነው፤ ሰው ሁሉ ያለመሥዋዕትነት እያገለገለ ባለበት መብቱን ክብሩን፣ ዕውቀቱን...... እየቆጠረ ሳለ ክርስቶስ አሁን ቢመጣ በጥቂቱ ታምኖ የሚያገኘውና በብዙ የሚሾመው አገልጋይ ስንት ይሆን?

በሉ እናንተ በብዙ ብላችኋልና ለአገልጋዮች ጌታ ልብ ይስጠን እያልኩ በዚሁ አበሁ::

ዶ/ር ደሴ ሺፈራው
ወላይታ ሶዶ

⇒ ውድ የእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች፣

የጌታ ጸጋና ሰላም ይበዛላችሁ፤ እውነት ጋዜጣ ቁጥር 2 ነች በመጀመሪያ እጄ የገባችው:: አነበብኳት በጣም ጠቀመችኛ:: አደራ የምላችሁ ነገር ቢ

*(ወደ ገጽ 20 ይዞራል)*

## የማስታረቅ .. ..ከገጽ 9 የዞረ

በብቻ መወጣት እንችላለን::

በእርግጥ አገልጋዮች እነርሱ ራሳቸው ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቁ አይችሉም፤ እግዚአብሔርም በእነርሱ የማስታረቅ ሥራን አይሠራም፤ ይህን ያደረገው በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ አይተናል፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የወንጌል አገልጋዮችን ወዳልዳነውና ወዳላመነው ሕዝብ የማስታረቅ ቃን አስይዞ ይልካል:: በሌላ አባባል እግዚአብሔር በመልእክተኞቹ በኩል ሕዝቡን ከእርሱ ጋር እንዲታረቁ ይማልዳል:: ከዚህም የተነሣ ሐዋርያው «እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለክርስቶስ መልእክተኞች ነን» ለማለት ተችሎታል/2ቆሮ5:20/::

ብዙዎቻችን ከእግዚአብሔር ጋር ለታረቁት ሰዎች የሚሆን የስብከት ቃን ለማቅረብ እንተጋለን፤ በተመቻቹ አዳራሾችና በተዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይ እየተጋበዝን በጭብጨባና በእልልታ እንደሚቀበሉን እርግጠኞች በሆንባቸው መድረኮች ለማገልገል እንሽቀዳደማለን፤ ይህ ግን የማስታረቅ አገልግሎት እንዳልሆነ አስተውለን እናውቃለንን? በእርግጥ እንደተሰጠን ጸጋ መጠን በእረኛነት፣ በአስተማሪነት ጌታ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያስነሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለታረቁ ሰዎች የሚያንጽ ቃን በማቅረብ ማገልገላችን የእግዚአብሐርን መግቦት ለልጆቹ ማቅረብ እንደሆነ የሚካድ አይደለም:: ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ሳይታረቁ አሁንም በቁጣው ሥር ያሉ እጅግ ብዙ ኢአማንያን ምድሪቱን እንደሞሏት ያስተዋልንና ወደ እነዚህ ሰዎች የማስታረቅ ቃን ይዘን ለመሄድ የምንፈቅድ የወንጌል አገልጋዮች ስንት ነን?



## እርሱ እግዚአብሔር ነው

በዚህ ክፉ ዘመን ክፋት በበዛበት
የሞት ፍርሃት በዝቶ ሥጋት ባየለበት
ጭንቅ- ጣር- ዋይታ- ኑሮ በሆነበት
እርሱ እግዚአብሔር ነው መሸሸጊያ አለት::

ትናንትናም ቢሆን
ዘመን ቢለዋወጥ
ታሪክ ቢገላበጥ
ምስክር ቢደመጥ
ማህደር ቢገለጥ፤
የታደገ እርሱ ነው የርሱ የሆኑትን
ያጽናና እርሱ ነው ፊቱ ያነቡትን::
የሃናን ልብ ሃዘን ማነው ያወቀላት?
ኤሊ ነው ሕልና ልቧን ያረጋጋት?
በአጋር መናቋን ለሣራ ያየላት
በስተ-እርጅናዋ በልጅ የባረካት
ከወንዝ የተጣለ ሙሴን የጋረደው
ለቅሶአቸውን አይቶ ሕዝቡን የታደገው
በአንበሶች ጉድጓድ ዳንኤልን ያየው
ፍጥረትን በሞላ የሚቆጣጠረው
ልብ ኩላሊትን ሚመረምረው
ባለማት ሁሉ ላይ ድንቅን የሚያደርገው
ዓይኑ ማይጋረድ እርሱ እግዚአብሔር ነው::

## የአዲስ ኪዳን.. ከገጽ 13 የዞረ

ኪዳንም ቢሆን የነበሩት መዘምራን በመድረክ ላይ ቆመው ፊታቸውን ወደ ሕዝብ አዙረው ለሕዝብ መዝሙር የሚያቀርቡ አልነበሩም፤ ክፍለ ዘመኑ ያለፈበት ያ የብሉይ ኪዳን አገልግሎት እንኳ መዘምራኑ መዝሙራቸውን ከሕዝቡ ጋር ወደ እግዚአብሔር የሚዘምሩ ነበሩ እንጂ ወደ ሕዝቡ የሚዘምሩና በፕሮግራም ላይ የመድረክ መዝሙር የሚያቀርቡ አልነበሩም፤ ስለሆነም የመዘምራን ቡድንን ማደራጀቱ ከብሉይ ኪዳን የመዘምራን አገልግሎት ጋር ለማመሳሰል ቢሞከርም በመድረክ ተሰልፎ ለሕዝብ ማቅረቡ ግን ከዓለማውያን የተውኔት ወይም የኪነት መድረክ የተኰረጀ እንደሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል:: እንዲያውም የመዘምራ ን ቡድን በመድረክ ከመቆማቸውም ሌላ «የሶሎ ዘማሪ» የሚባሉ ግለሰቦችም በየመድረኩ እየቆሙ መዝሙር የሚያቀርቡበት ሥርዓትም በብዛት ይታያል:: ይህ ደግሞ በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም ፈጽሞ የማይገኛ ዓለማዊ ሥልትን የተከተለ ፋሽን ነው:: በዓለማዊነት ተጽዕኖ ሥር የወደቀ አምልኮ ደግሞ ለእግዚአብሔር አይስማማውም:: በመሠረቱ ሕዝቡ እንደቤተክርስቲያን የሚሰበሰበው በመዝሙር እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው እንጂ የመዘምራንን መዝሙር ሊያደምጥ አይደለም፤ አዳዲስ መዝሙሮችን ለማጥናት ከሆነ ግን ያን የምናደርገው በአምልኮ ጊዜ መሆን የለበትም:: መዝሙሮችን ለማጥናት በተመደበ ጊዜ በመገኘት አሊያም በየካሴቱ በቤት ውስጥ በማድመጥ መዝሙሮችን ማጥናት ይቻላል:: በአምልኮ ጊዜ ግን አንዱ ያመጣውን መዝሙር ሁሉም አማኛ በአንድ ልብ ሆኖ በመንፈስ ሊዘምረው ይገባል:: መንፈስ ቅዱስም ይህን አምልኮ የተስማማና የሰመረ አምልኮ ያደርገዋል::

## የተለዩ አልባሳትን በመልበስ ማገልገል

በአምልኮ ጉባዔ ጊዜ ሁላችንም በአንድ መንፈስ ሆነንና በክርስቶስ አካል ውስጥ ባለንበት የብልትነት ስፍራችን ሆነን ልናመልክ ይገባናል:: አንድ ብልት ከሌላው ብልት አይበልጥም፤ አንድ ብልትም ከሌላው አያንስም:: የብልቶች ሁሉ ራስ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው፤ በመሆኑም ከኢየሱስ በቀር እኛን በመወከል በእግዚአብሔር ፊት ሊቀርብ የሚችል ማንም የለም፤ በመካከላችን የሚያገለግሉ ሰዎች በአምልኮ ጊዜ እንደማንኛውም ብልት አብረው ያመልካሉ እንጂ አምልኰውን ሊመሩም ሆነ ጉባዔውን በእግዚአብሔር ፊት ሊወክሉ አይችሉም:: ከዚህም የተነሳ ለየት ብለው እንዲታዩ የሚያደርጋቸውን ምንም ዓይነት ነገር ማድረግ የለባቸውም::

በአምልኮ ጉባዔ ጊዜ አስመላኪዎች የሚባሉትም ሆኑ ቀዳሽያን ተብለው የሚታወቁት ሰዎችና የመዘምራን ቡድን ተብለው ከአዲስ ኪዳን መሠረታዊ የአምልኮ መመሪያ ውጪ የሚመደቡት ሰዎች የተለዩ አልባሳትን ለብሰው እንዲያገለግሉ ማድረግ ከሕዝቡ ለየት ብለው እንዲ ታዩ ከሚያደርጓቸው ነገሮች አንዱ ነው:: ይህም የተለዩ አልባሳትን ለብሶ የተለየ የአምልኮ አገልግሎትን መፈ ጸም በዘመናችን በብዙ ቦታዎች የሚታይ ቢሆንም የተቀዳው ከአዲስ ኪዳን ሳይሆን ያው የተለዩ ካህናትና ሊ.ቃ ካህናት መሥዋዕትን ያቀርቡበትና የተለዩ መዘምራን ያገለግሉበት ከነበረው ከብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ነው:: በብሉይ ኪዳን በቤተመቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ የሚለብሱት የተለዩ አልባሳት እንዲኖራቸው ታዝዟል:: ለምሳሌ አሮንና ልጆቹ /ሊቀካህኑና ካህናቱ/ የሚለብሷቸው የተቀደሱ ልብሶች በዘጸአት 28 ተገልፀዋል:: እነርሱም የደረት ኪስ፣ ኤፉድ፣ ቀሚስ፣ ዝንጉርጉር ሸሚዝም፣ መጠምጠሚያ እና መታጠ ቂያ ናቸው/ዘጸ28:1-5/፤ እንዲሁም ቆቦቹንና የተቀደሰውን አክሊልም ያደርጉ ነበር/ዘጸ40:40፣ 29:6/፤ ከሊቀካህኑና ከካህናቱም ሌላ በመቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ የሚለብሷቸው አልባሳት ነበሩ:: መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም አጠሎ ሲ ገልጥ «በመቅደስ ውስጥ ለማገልገል በብልሃት የተሠሩትን ልብሶች፣ በክህነት ያገለግሉበት ዘንድ የተቀደሱትን የካህኑን የአሮን ልብሶች፣ የልጆቹንም ልብሶች» ያደርጉ ዘንድ እንደታዘዙ ይገልጻል/ዘጸ35:19/፤ ሆኖም ከክህነትና ከመቅደስ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የተሰጠው ይህ የአልባሳት ሕግ ከክህነቱና ከመቅደሱ አገልግሎት ጋር አብሮ ቀርቷል፤ በዘመነ ሐዋርያት የተለዩ አልባሳት እየለበሱ አምልኰን የሚመሩ ሰዎች አልነበሩም፤ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን የብሉይ ኪዳን ሥርዓተ አምልኰን በቤተክርስቲያን ውስጥ አንዳንዶች እያስገቡ ሲመጡ በአምልኮ ጊዜ ከሕዝቡ ተለይተው ካህናት የሚባሉ መሪዎችን ከማቆም ጀምሮ እነዚሁ መሪዎች የተለዩ አልባሳትንም እንዲ ለብሱ ማድረግ ተጀመረ:: ሆኖም አስቀድሞ እንደተመለከትነው አማንያን ሁሉ መንፈሳዊ መሥዋዕትን የሚያቀርቡ ካህናት ናቸው፤ ስለሆነም የተወሰኑ ሰዎችን ከሌሎች የሚለይ የክብርና የጌጥ ልብስ በአዲስ ኪዳን አማኞች ዘንድ ፈጽሞ ሊኖር አይገባም::

በአንድ በኩል «ካህናት» ወይም «ቄሶች» እየተባሉ በሌላ በኩል ደግሞ «አስመላኪ» እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች ከሕዝብ ተለይተው የሚለብሱት የተለየ ልብስ ካለ ግን ያው በብሉይ ኪዳን የአገልግሎት ሥርዓት ሥር መውደቅ ነው:: ከዚህም ይልቅ ደግሞ ከሕዝብ የተለዩ መዘምራን በሚቆሙባቸው ጉባዔያት ውስጥ የመዘምራን ልብስ መዘምራኑን ከሕዝቡ ለይቶ ለማሳየት እያገለገለ ይገኛል:: በብሉይ ኪዳን ከዳዊት ዘመን ጀምሮ መዘምራን እንዳሉ ብናነብም ስለ መዘምራን ልብስ የምናነበው ል ግን የለንም፤ ሆኖም በዘጸ35:19 ላይ እንዳየነው በመቅደስ የሚያገለግሉ ሁሉ የተለየ ልብስ ስለነበራቸው በቡድን የሚደራጁት «ሌዋውያን መዘምራንም» የተለየ ልብስ ሊኖራቸው እንደሚችል እንረዳለን፤ በአንዳንድ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ውስጥ በ2ዜና20:21 ላይ ኢዮሣፍጥ ከሞዓባውያንና ከአሞናውያን ጋር በተዋጋ ጊዜ እግዚአብሔርን እንዲ ያመሰግኑ ያቆማቸው መዘምራን ጌጠኛ ልብስ ለብሰው እንደነበር ተገልጧል፤ ይህም ቢሆን በጦር ሜዳ እንጂ በቤተመቅደስ እንዳልነበር ሊስተዋል ይገባል::

በአዲስ ኪዳን ግን ከምእመናን መካከል የተለዩ መዘመራን ስለመኖራቸው የምናነበው ነገር እንደሌለ ሁሉ የተለየ የመዘምራን ልብስ ስለመኖሩም በአንድም ሥፍራ አናነብም:: በአዲስ ኪዳን የምእመናንም ሆነ ከምእመናን መካከል በጸጋ የሚገለጡ አገልጋዮች ሁሉም በአንድነት የሚለብሷቸው ልብሶች ምን ምን እንደሆኑ ተገልጧል፤ በሮሜ13:14 እና በገላ3:27 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የአማኞች ልብስ እንደሆነ ሲገልጥ በቈላ3:12-14 ደግሞ ምሕረትን፣ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትህትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግስትን እንዲሁም የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን እንድንለብስ ታዝዘናል:: ከዚህ በተረፈ እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን በአምልኮ ጊዜ አንዳንዶችን ከሕዝብ ለየት ብለው እንዲታዩ የሚያደርጉና የተቀደሱ የሚባሉ፣ ያሸበረቁና ጌጠኛ የሆኑ የጨርቅ አልባሳት እንዲኖሩን አልታዘዝንም:: ስለሆነም ከብሉይ ኪዳን የአገልግሎት ሥርዓት ተጽዕኖ ተላቅቀን እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ብቻ ልናመልከው ይገባናል:: በዓይናችን ፊት የሚታዩ ጌ ጠኛ አልባሳትን የለበሱ ሰዎች በሌሉበት በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እየተመራን ■

### የእግዚአብሔር ዓይኖች

ጽድቅን ባለማወቅ በኃጢአት ሳለሁŸ
የምኖር ሰው ነበርኩ ሞት እንደከበበŸ
አሁን ግን ድኜአለሁ፤ የአየሱስ ሆኜአለሁ
በእግዚአብሔር ዓይኖች በእርግጥ ታይቻለሁ

ጠላት ሲፈትነŸ መከራ ቢያሳየŸ
ጭንቀቴን አብዝቶ በሞት ቢያስፈራራŸ
ሕይወቴም ሲለወጥ ሁሉ ቢፀየፈŸ
የእግዚአብሔር ዓይኖች ግን ከሰማያት አየŸ

ከእንግዲህ ሁላችን ስንኖር በምድር ላይ
እስከመጨረሻው እንሁን አስተዋይ
ሊያጠን አይችልም ያ ክፉ አታላይ
የእግዚአብሔር ዓይኖች ስላሉ በኛ ላይ

## የአንባብያን.. ከገጽ 14 የዞረ

ኖር «በእንዲህ ያለ ቦታ እንዲህ ያለ ኰንፈረንስ ተካሄደ»፤ «ይህን ያህል ሰው ጌታን ተቀበለ» ወደሚል ሪፓርት ሳትገቡ እንደ ጀመራችሁት እንዲሁ ሉን በማስተማርና በሉ መስተዋትነት ሰዎች ራሳቸውን እንዲመለከቱ በመርዳት ቀጥሉ ነው። ጌታ ይባርካችሁ።

ሰሎሞን ኪዳኔ
ሐረር

⇒ በጌታ እጅግ ስተወደዳችሁ ስእውነት ጋዜጣ አዘጋጆች በሙሉ

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላም ለሁላችሁ ይሁን አሜን።

ጋዜጣዋን እኔ ያየሁት በቅርብ ነው። የከበረና የጊዜውን የእግዚአብሔር ሐሳብ ይዛ ብቅ ብላለች፤ በጣም ደስ ብሎኛል ጌታ ይባርካችሁ፤ በዚህች ጋዜጣችሁ ያየሁት በመጀመሪያ የራሴን ሕይወትና አገልግሎት ነው። በመቀጠልም የሌሎችን ሰዎች ሁሉ ሕይወት ሊጠቅም የሚችል ልን እንደያዘች ለመረዳት ችያለሁ፤ እንደ አጀማመራችሁ ወደፊት ይበልጥ በማሻሻል እንድትቀጥሉ ጸሎቴ ነው። የጌታ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን።

ብርሃኑ ነጋሽ
ጂማ

■

## እንነሣና .. ከገጽ 15 የዞረ

ጀምሮ በረከሱ ተግባራት እስከመገለጥ ድረስ የሚታየው የቅጥር መፈራረስ ከልብ አያሳዝንምን? ቅጥሩንስ ለመሥራት የሚቀርበውን ማናቸውንም ጥሪ ተቀብለን «እንነሣና እንሥራ» ለማለት ጊዜው አይደለምን?

በእርግጥ በወንጌል ሥራ አብዝተው የሚሮጡ ሰዎችን መልካም እያደረጋችሁ ነው አይዞአችሁ በርቱ ማለት ይቻል ይሆናል፤ በዚህ ዘመን ግን ከሁሉም የሚያስፈልገው «እንነሣና እንሥራ» የሚል ቁርጠኛ ውሳኔ ነው። ሆኖም በዚህ ዓይነት ሁላችንም አብረን ለመሥራት መፍቀዳችንን መግለጥ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ማሳየት ይገባናል፤ ለነህምያ ምላሽ የሰጡት የአይሁድ ቅሬታዎች «እንነሣና እንሥራ» በማለት ብቻ አላበቁም፤ ይሁንና «እጃቸውንም ለበጎ ሥራ አበረቱ» ተብሎ እንደተጻፈ ተግባራዊ ሥራውን ወዲያውኑ ሲጀምሩ እንመለከታለን /ነህ2፡18/፤ ስለዚህ በዚህ ዓለም ባለው ክፋት እየተጠቁ ያሉና መንፈሳዊ ቅጥሩ የፈረሰ መሆኑን የተረዱ አማኞች እንነሣና እንሥራ ከሚለው የቃል ምላሽ በተጨማሪ ቅጥሩን ለመሥራት የሚያስችል ተግባራዊ ምላሽም ይጠበቅባቸዋል። እያንዳንዳቸው የእግዚአብሔር ቃ በልበ ሰፊነት በመመርመር ጠላት ያፈረሰውን ቅጥር እንደገና ለመሥራት በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ሊነሣሱና ሊሠሩ ይገባቸውዋል። በዚህ ዘመን ጠላት ያፈራረሰውን አማኞችን ከዓለም የሚለየውን ቅጥር እንደገና መሥራት እንዴት ይቻላል? ክርስትና እንደመጀመሪያዎቹ አማኞች ሊሆንልን እንዴት ይችላል? በዚያን ጊዜ የነበረውን አንድ ልብ፣ እውነተኛ ፍቅርና ቅድስና መልሶ ማምጣት እንዴት ይቻላል? በእግዚአ ብሔር ከተማ ውስጥ በድፍረት ለሚኖሩ የክፋት መልእክተኞች ይህ የማይቻል ይመስላቸዋል። «ይቻላል» ሲባሉ ደግሞ ነገሩ ያስቋቸዋል። ሖሮናዊው ሰንባላጥ፣ ባሪያውም አሞናዊው ጦቢያ፣ ዓረባዊውም ጌሣም በነህምያ ላይ ይስቁ ነበር፤ ቀላልም አድርገው ቆጥረዋቸው ነበር። ይሁን እንጂ ነህምያ «የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን እናንተ ግን በኢየሩሳሌም እድል ፈንታ የላችሁም» አላቸው /ነህ2፡20/። በዘመናችን «እንነሣና እንሥራ» በማለት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት በቅንነት በተነሣን ጊዜ ይህ እንዴት ይቻል? ብለው ለሚስቁብን ሁሉ «የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን» ከሚለው ከዚህ ድንቅ መልስ የሚበልጥ ሌላ ምን መልስ ይኖረናል?

●

**ያለ ዋጋ የተቀበላችሁትን ያለዋጋ ስጡ/ማቴ10፡8/።**

«እውነት» በየሁለት ወሩ የሚታተም የክርስቲያኖች ጋዜጣ ነው። አሳታሚው ለጋዜጣውም ሆነ ለሌሎች መጻሕፍት የሚሰጠው የዋጋ ዝርዝር የለም፤ ለሚልካቸው ህትመቶች ሁሉ ዋጋ አይጠይቅም፤ ለማንበብ የሚፈልግ ሁሉ ዋጋ እንዲከፍል ሳይገደድ ፍላጎቱን በመግለጥ ብቻ ሊያገኛ ይችላል፤ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ በበጎ ፈድ የገንዘብና የእውቀት አስተዋጽዖ የሚካሄድ የጸጋ አገልግሎት ነው፤ በዚሁ መልክ ጋዜጣውንም ሆነ ሌሎችን መጻሕፍት ለብዙዎች ማዳረስ እንድንችል እግዚአብሔር ልቡን ያነሳሳው አማኛ በፖስታ ቤት <u>በሐዋላ</u> ለአሳታሚው የገንዘብ አስተዋጽዖውን መላክ ይችላል።

እግዚአብሔር በጸጋ ያለዋጋ ከሰጠው የሉ ማዕድ ተካፋይ ለመሆን የምትሹ ሁሉ የሚከተሉትን ህትመቶች በመጻጻፍ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፤

1.ደብተራ ኦሪት
2.የዕብራውያን መልእክት አንድምታ
3.መካነ ህሩያን
4. ጦማረ ጽድቅ
5. የኦሪት ዘፍጥረት ትርጓሜ
6.መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው መለኮት
7.የአዲስ ኪዳን መካከለኛ
8.የኦሪት ዘጸአት ትርጓሜ
9.መጽሐፈ ሰዓታት በመቅደሱ ሚዛን
10. ለጀማሪ አማኞች የሚረዳ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ናቸው።

መጻሕፍቱንም ሆነ ጋዜጣውን ስማግኘት በአሳታሚው አድራሻ በመጻፍ ይጠይቁ
*ወይም*
በሚቀጥሉት ስልክ ቁጥሮች ይደውሉ፤

| | |
|---|---|
| አሰላ | 02-311312 |
| ጎባ | 06-610779 |
| ጂማ | 07-112357 |
| ደ/ብርሃን | 01-813147 |
| አዲስ አበባ | 01-774677 |
| በደሌ | 07-450365 |
| ዲላ | 06-310384 |

### <u>ማሳሰቢያ</u>

1.ከዚህ ቀደም ከእነዚህ መጻሕፍት በከፊል ተጻጽፋችሁ ያገኛችሁ አንባቢያን መጠየቅ የምትችሉት ያልደረሷችሁን መጻሕፍት ብቻ መሆኑን እንገልጻለን፤

2.ጥያቄ ወይም አስተያየት ያለው ሰው በአድራሻችን ቢጽፍልን የምናስተናግድ መሆናችንን እንገልጻለን፤

3. ከአንድ በላይ መጻሕፍት እንዲላኩላችሁ የ ጠየቻችሁ በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ መ ጽሐፍ የማንልክ መሆኑን እንገልጻለን፤ ሆኖም የተላከላችሁን አንብባችሁ ስታበቁ ቀጣዩን በመ ጠየቅ ማግኘት ትችላላችሁ።

4. ጥቅሶች ከመዝሙረ ዳዊት ሲጠቀሱ የምዕራፍ ቁጥር በቅንፍ የሚገኘው ነው።

**ቴምብር/ STAMP**

**COPY RIGHT© BGNLJ**
**`EUNET´ IS PUBLISHED BY : BGNLJ – NON PROFIT ORGANIZATION DEVOUTED TO THE PROPAGATION OF BIBLE TRUTH, P.O.Box 14787, ADDIS ABABA, ETHIOPA**

**ላኪ**/SENDER

BGNLJ
**ፖ. ሣ. ቍጥር** 14787
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**
**BGNLJ**
P.O.Box 14787,
ADDIS ABABA, ETHIOPA.

**ለ**/To ____________